# አዲስ ዘመን

እንድ

ማክሰኞ | 81ኛ ዓመት ቁጥር 319 ሐምሌ 19 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# የኢትዮጵያዊነት ጥግ በዓለም አደባባይ ሲገለጽ



ቦጋለ አበበ

መላው ኢትዮጵያውያን ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የደስታ ስሜት አልራቃቸውም። የደስታቸው ምንጭ ምን ይሆን ብሎ? ለሚጠይቅም መልሱ አጭርና ግልጽ ነው፤ እንቁ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች። በትውልድ ቅብብሎሽ የደመቀው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ዓለም አቀፍ የአትሌቲክስ ድልና ኢትዮጵያዊነት አንድ ናቸው።

‹‹የሉም፣ ተዳክመዋል፣ ከስመዋል›› ሲባሉ ይበልጥ ይጎላሉ። ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአሜሪካ ኦሪገን ሲካሄድ የሰነበተው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናም ይህን እውነት በገሃድ አውጥቶታል። ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የገጠማት ጦርነት እንዲሁም በተለያዩ አካባቢዎች የሚከሰቱ ግጭቶችና የንፁሃን ዝጎች ግድያ እንኳን በዓለም ታላቅ የስፖርት መድረክ ጎልታ መታየት ይቅርና ተሳታፊ

የኢትዮጵያዊነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


pepsi


# “በውስጥና በውጭ የገጠመንን ፈተና ለመሻገር እንደ ሕዝብ አንድነታችንን በማጠናከር መረባረብ አለብን”

-ዶክተር ይልቃል ከፋለ
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር



በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በውስጥና በውጭ የገጠመንን ፈተና ለመሻገር እንደ ሕዝብ አንድነታችንን በማጠናከር መረባረብ አለብን ሲሉ የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር አስታወቁ፡፡ በክልሉ በተወሰደው የሕግ ማስከበር ዘመቻ ሕዝቡ እፎይ ማለቱንም ገልጸዋል፡፡

ርእሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ የአማራ ክልል ምክር ቤት መደበኛ ጉባዔ ትናንት በባህርዳር ከተማ ሲጀመር እንደገለጹት፤ የአማራ ክልል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተጋረጠበትን ውስጣዊና ውጫዊ ፈተና ለመሻገር አንድነቱን ማጠናከር አለበት፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ እንደገለጹት፤ መንግሥት እስካሁን ባደረገው የሕግ ማስከበር እንቅስቃሴ በልዩ ልዩ ወንጀሎች የተጠረጠሩ 10 ሺህ 981 ተጠርጣሪዎች ተይዘው ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ተጣርቶ በርካቶች ተለቀዋል። በሕግ ማስከበር ዘመቻውም ሕዝቡ እፎይ ብሏል፡፡ የተጀመረው ስራም ተጠናክሮ ይቀጥላል።

የአማራ ክልል የተረጋጋ እንዲኾን እየተሠራ መኾኑን የገለጹት ዶክተር ይልቃል፤ የነበረውን የፀጥታ ችግር በመቋቋም ወደ ልማት መመለስ መቻሉንም አስታውቀዋል

የትህነግን ወረራ ለመቀልበስ፣ ከፍተኛ ርብርብ መደረጉንና አሁንም ጥረት እያደረገ መሆኑን የጠቀሱት

“በውስጥና በውጭ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


አርሾ
ሜዲካል ላቦራቶሪ ኃ.የ.ተ.የግ.ማ
ARSHO MEDICAL LABORATORIES PLLC
በትውልድ የታመነ!
አድራሻ - አራት ኪሎ፣
ከአራዳ ክፍለ ከተማ ሕንፃ ጀርባ፣
የ24 ሰዓት አገልግሎት
612
0114-16-70-89
0911-10-18-18




## “አትሌቶቻችን በጠንካራ የቡድን መንፈስ የተጎናጸፉትን ድል በሌሎችም መስኮች መድገም ያስፈልጋል”

- አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ

ገጽ 4


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር
የበረንዳ ታይልስ ኢጋ መደበኛ ኩልሞ
0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA
ሕብረት ኢንሹራንስ አማ
THE UNITED INSURANCE COMPANY SC
Tomorrows Company Today'
ለህይወት ህጋዊ ግዴታዎ ለንብረት
ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ
+251 111 26 34 34
united.insurance@unic-ethiopia.com
7469

# በክልሉ 295 ሺህ ተፈናቃዮች ወደቀዬአቸው መመለሳቸው ተገለጸ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ከተፈናቀሉ 300 ሺህ የአፋር ክልል ተፈናቃዮች 295 ሺህ ያህሉ ወደቀዬአቸው መመለሳቸውን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአካባቢው ባለሥልጣናት አስታወቁ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ አስተባባሪን በመጥቀስ ቪኦኤ እንደጠቀሰው፤ የሕወሓት ቡድን በአፋር ክልል ለወራት የዘለቀ የጅምላ ግድያ፤ አስገድዶ መድፈር፣ ዘረፋ እና የመሰረተ ልማት ውድመት ሲያደርስ ቆይቷል። በዚህም የሚፈፀመውን ግፍ በመሸሽ ከቀዬአቸው ተፈናቅለው ከነበሩ 300 ሺህ ከሚጠጉ ተፈናቃዮች ውስጥ በተሠሩ ተከታታይ ሥራዎች 295 ያህሉን ወደቀዬአቸው መመለስ ተችሏል።

በአሸባሪው የሕወሓት ቡድን ለወራት ተይዛ የነበረችው በአፋር ክልል የምትገኘው ኮናባ ከተማ ምንም እንኳን አሁን ላይ ነዋሪዎች እየተመለሱና እንደገና እየገነቧት ቢሆንም ቡድኑ ምድረበዳ አድርጓት እንደሄደ ነው ድርጅቱ የጠቀሰው፤ በርካታ የሆኑ የከተማዋ ነዋሪዎች ቤቶች፤ የንግድ ተቋማት እና ሌሎችም በቡድኑ በእሳት ወድመዋል፤ ተዘርፈዋል ብሏል።

በርካታ ነዋሪዎች ወደቀዬአቸው መመለሳቸውን የገለጹት፤ የኮነባ ከተማ አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ መሐመድ አብዱላ ሆኖም ቤቶቻቸው በቡድኑ ከመዘረፋቸውም ባሻገር ነዋሪዎቹ ሊገበያዩበት የሚችሉት ገበያና ሱቆች የሉም፤ በአካባቢው ከፍተኛ የሆነ ረሀብ ተከስቷል፤ በርካታ ሕፃናትም በርሐብና በምግብ እጦት እየተሰቃዩ ነው ብለዋል።

እንደዘገባው ከሆነ፣ ወደ አካባቢያቸው ከተመለሱት አንዷ የሆነችው የበረሃሌ ነዋሪ ሲቲና አብደላ፤ በሰኔ ወር ልጇን ይዛ የተመለሰች ናት። ሲቲና እንዳለችው የሕወሓት ቡድን ወደከተማቸው ሲገባ ሀብት ንብረቷንና ያሏትን እንስሳት ጥላ ሕይወቷን ለማትረፍ ነው አካባቢውን ለቃ የወጣችው። አሁን ወደ ቀዬዋ ተመልሳለች፤ ነገር ግን ቡድኑ የሚችለውን ዘርፎ ቀሪውን ደግሞ አቃጥሎ በመሄዳዱ ስትመለስ ያገኘችው ምንም ነገር እንደሌላት ትናገራለች።

በአፋር ክልል የኢረብቲ ከተማ አስተዳደሪ መሐመድ አሊ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ በከተማዋ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ውድመት ደርሷል። በአካባቢው መብራት ባለመኖሩ ቀደም ሲል መብራት ሲጠፋ ይገለገሉበት የነበረውን ጀነሬተር ነው እየተጠቀሙ ያሉት።

እንደ አቶ መሐመድ ገለፃ፤ በኢረብቲ ከተማ የመብራት፣ የኢንተርኔት እና ሌሎች የመገናኛ ዘዴዎች በሕወሓት በደረሰባቸው ከፍተኛ ውድመት ሁኔታዎች ሁሉ አስቸጋሪ ሆነዋል። ሆኖም በአካባቢው የበጎ አድራጎት አገልግሎት የሚያደርጉ አካላት ነበሩ። እነዚህ በጎ አድራጊዎች የውሃ አቅርቦት እና መሰል አገልግሎቶችን ለማሕበረሰቡ እየሰጡ ቆይተዋል ብለዋል።

የበርሃሌ አስተዳዳሪ የሆኑት አቶ ከድር ሁሴንም፤ በበርሃሌ ከተማ በርካታ የጤና ተቋማት በሕወሓት ቡድን ውድመት እንደደረሰባቸው ተናግረዋል። ለማሕበረሰቡ አገልግሎት ይሰጡ የነበሩ 16 የጤና ተቋማትም ወድመዋል ብለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ በአፋር ክልል ከተፈናቀሉበት ወደ ቀዬአቸው የተመለሱ ዜጎች የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ገልጿል።

# በዘርፉ የሚታዩ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ለመፍታት የንግድ ፖሊሲ በመዘጋጀት ላይ መሆኑ ተገለጸ

**በኃይሉ አበራ**

አዲስ አበባ፡- ከንግድ አንጻር ያሉብንን በርካታ ክፍተቶች ለመሙላት የሚስችል ፖሊሲ ተዘጋጅቶ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር ገለጸ።

“ኢትዮጵያ እያሸነፈች ትሻገራለች”፤ በሚል በጅማ ከተማ በተካሄደው ስለኢትዮጵያ መድረክ ላይ የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ዴኤታው አቶ እንዳለማው መኮንን ባቀረቡት የመነሻ ሃሳብ እንደገለጹት፤ አንድ ሀገር የተፈራ እና የተከበረ እንዲሆን ጠንካራ መከላከያ ያስፈልገዋል፤ ጠንካራ መከላከያ ጠንካራ ኢኮኖሚን ይፈልጋል፤ ጠንካራ ኢኮኖሚ ዜጎች በሰላም ወጥተው ገብተው፣ ሰርተው፣ ግብር ገብረው የሚኖሩበት የተደላደለ ነገር ማድረግ የሚችል ጠንካራ መንግሥት ያስፈልጋል። ጠንካራ መንግሥት ጠንካራ ፖሊሲ ያስፈልገዋል።

ባለፉት ጊዜያት እንደ ሀገር ንግዱን የምንመራበት ጠንካራ የንግድ ፖሊሲ አልነበረንም ያሉት ሚኒስትሩ ላለፉት 60 ዓመታት የነበረው ኮሜርሻል ኮድ ወይም የንግድ ሕግ ሶስት የተለያየ ባህሪ ያላቸው መንግሥታትን ያስተናገደ ነው ብለዋል። ቴክኖሎጂ ባደገ ቁጥር ብዙ የተለወጡ ነገሮች ቢኖሩትም መለወጥ ያልቻለና ዜጎች በአነስተኛና በመካከለኛ ደረጃ ንግድን በቀላሉ ጀምረው በቀላሉ የማይለወጡበት በሩቁ የሚፈራ እንደነበርም ጠቁመዋል።

በአዲሱ ሪፎርም ጠንካራ ፖሊሲና ጠንካራ ሕግ ስለሚያስፈልገን ያንን በመፈተሽ ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የንግድ ሕግ በአዲስ መልክ ተዘጋጅቶ መቅረቡን ገልጸዋል።

በዚህም አምስት መጽሐፍ የነበረው ሁለት መጽሐፍ ሆኖ በነዚህ ሰነዶች አጠቃላይ ስለንግዱ የበለጠ ለማወቅ የሚቻል መሆኑን ጠቁመዋል።

የንግድ ፖሊሲን በተመለከተ ንግድ የሚመራበት ፖሊሲ አልነበረንም ያሉት አቶ እንዳለማው፤ አሁን የመጨረሻ ረቂቅ ተጽፎ ለማጸደቅ በሂደት ላይ የሚገኝና ላለፉት 10 ወራት በትኩረት ሲሰራበት የቆየ ነው ብለዋል።

ይህም አንደ ሀገር በንግድ ሥርዓት ውስጥ ያሉትን ቁልፍ ችግሮችን ሊፈታ የሚችሉ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዙ 11 ምዕራፎችን የያዘ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ጠንካራ የንግድ ፖሊሲ ሲኖር አሁን የሚታየው የንግድ ምስቅልቅል እና ወጣገባ አሰራር ሊፈታ የሚችል እምነት አለኝ ብለዋል።

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከውጭ የምታስገበው ገቢ ወደ 18 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር መሆኑን የጠቆሙት አቶ እንዳለማው፤ በአንጻሩ ከወደውጭ ልካ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ደግሞ ከአራት ቢሊዮን ብዙም ያልዘለለ መሆኑን ጠቁመው ይህም የንግድ ሚዛኑ ላይ ወደ 15 ቢሊዮን ዶላር ልዩነት መኖሩን እንደሚያሳይ አንስተዋል፡፡ በመሆኑም የንግድ ልዩነት ማጥበብ ላይ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ አመላክተዋል።



ፎቶ - ዳኜ አበራ

አቶ እንዳለማው መኮንን

ባለፈው ዓመት በሀገራዊ ችግር ውስጥ ቢንሆንም በ2014 በጀት ዓመት የወጪ ንግዱን ወደ አራት ነጥብ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ማድረስ መቻሉን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ጠንክረን ከሰራን እና ጠንካራ ተቋማት መገንባት ከተቻለ ከዚህም በላይ ማድረስ ይቻላል ብለዋል።

በጠንካራ የኤክስፖርት ስትራቴጂውም ቀጥታ ከግብርና የሚወጣውን እና እሴት ተጨምሮበት ከፋብሪካ የሚወጣውን ምርት በአይነት በመጨመር አሁን ወደ ውጭ የሚላከውን ምርት በዓይነት ማስፋት አንዱ አቅጣጫ አድርጎ ይዟል ብለዋል።

በቀጣይ አሁን የተለመዱትን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የገበያ መዳረሻዎችን ማስፋት እንደሚገባ በመግለጽም የአገዋ ገበያ ተጽዕኖን በምሳሌነት አንስተዋል።

የማምረት አቅም ማሳደግ ከተቻለ እና የተቀባይ አገራት በሚፈልጉት ደረጃ ጥራት አሟልተን ምርት ማቅረብ ከቻልን የአጉዋ ዓይነቱን የማበረታቻ ገበያን መለማመጥ የማያስፈልግ መሆኑን አመላክተዋል።

አሁን ካለው የገበያ ውድድር ይልቅ መጪው የሀገራት ዝግጅት ያስፈራል ያሉት አቶ እንዳለማው፤ ሲሉም ሲንጋፖር ስድስት በመቶ የዓለም ገበያ ድርሻ ሲኖራት የአፍሪካ 55 ሀገራት ተደምሮ ሁለት በመቶ የማይሞላ መሆኑን አንስተዋል።

በመሆኑም በዚህ ላይ ለውጥ ለማምጣት የተለየ ዕይታ እና ክሒሎት የበለጠ መስራት የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

አሁን ዘመናችን በምትገኝበት አራተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ተወዳዳሪ ለመሆን ሶስት ነጥብ አምስት ትሪሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገበያ ያለው እና አንድ ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ሕዝብ ያለበትን የአፍሪካ ነጻ የንግድ ቀጠና አባልነት እንዲሁም የዓለም የንግድ ድርጅት አባልነት እንቅስቃሴ ላይ አጠናክሮ መስራት የሚጠይቅ መሆኑንም አፅዕኖት ሰጥተዋል።

# በፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች የሚደርስ ጉዳትን ለማስቀረት አዲስ ማስተር ፕላን ሊዘጋጅ መሆኑ ተጠቆመ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመንገድ ዳር ፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች የሚደርስ ጉዳትን ለመቅረፍ አዲስ የከተማ ማስተር ፕላን ለማውጣት እቅድ መያዙን የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ገለጸ።

የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳሬክተር የሆኑት አቶ እያሱ ሰለሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ በአዲስ አበባ የመንገድ ዳር ፍሳሽ ማስወገጃ አጠቃቀምና አጠቃላይ ሁኔታ እጅግ በጣም አሳሳቢ እየሆነ ነው።

በተለይ በክረምት ወቅት እየደረሰ ባለው የጎርፍ ችግር በርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለችግር እየተጋለጡ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም የትራፊክ ሁኔታውም እየታወከ የመጣበትና የአስፋልት መንገዶች ለከፍተኛ ብልሽት እየተዳረጉ ያለበት ሁኔታ ላይ ነን ብለዋል።

ስለዚህ የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን ይህንን ሁኔታ ተመልክቶ በየጊዜው መፍትሄ ለመስጠት እየሞከረ መሆኑን ጠቁመዋል፤ ለአብነትም በበጋ ወራት 320 ኪሎ ሜትር የሚደርስ የመንገድ ዳር ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር የጽዳትና ጥገና ስራ ሲሰራ ቆይቷል ብለዋል።

ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሆኑ ቦታዎችን ደግሞ ለይቶ የመስራት ስራዎች በየአመቱ ሲሰራ የቆየ ቢሆንም ለከተማዋ በቂ አለመሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ እያሱ ማብራሪያ፤ አዲስ አበባ የመንገድ ዳር ፍሳሾችን ማስወገጃ ማስተር ፕላን የላትም። ስለዚህ ማስተር ፕላን ኖሯት በአግባቡ የሚመራ የመንገድ ፍሳሽ ማስወገጃ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ከዓለም ባንክ ጋር በጋራ በመሆን የመንገድ ዳር ፍሳሽ ማስወገጃ ማስተር ፕላን ጥናት ለማድረግ መታቀዱን ዳሬክተሩ ተናግረዋል።

ይህ ጥናት ሙሉ በሙሉ ተጠናቆና ጸድቆ ወደ ተግባር እንዲገባ የአዲስ አበባ ከተማ መንገዶች ባለሥልጣን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ መሆኑንም ተናግረዋል።

ነገር ግን አሁን ባለው ሁኔታ በጃችን ያለውን የፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ደሕንነት ጠብቀን በአግባቡ ከተጠቀምንበት አሁን እየገጠመን ያለውን ችግር በከፍተኛ ሁኔታ ለመፍታት የሚያስችል እድል መኖሩን ጠቁመዋል።

ይህን ችግር ለመፍታት ጥረት ስናደርግ የሚገጥመን ችግሮች አሉ ያሉት አቶ እያሱ፤ በተደጋጋሚ ሕብረተሰቡ በመንገድ ዳር ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ላይ ደረቅ ቆሻሻ ሲጥልና ማስወገጃ መስመሩን ለብልሽት የሚያጋልጡ እንቅስቃሴዎች ሲያደርጉ ይታያሉ ብለዋል።

በተለይ የመንገድ ፍሳሽ ማስወገጃ መስመር ላይ መኪና የማቆምና በመንገድ ዳር ላይ የግንባታ ቁሳቁሶችንና ተረፈ ምርቶችን አስቀምጦ የግንባታ ስራዎችን ማከናወንና በጎዳና ላይ ከሚደረጉ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሚመነጩ ቆሻሻዎች በራሱ ወደ ፍሳሽ ማስወገጃ የሚገቡ በመሆኑ በተደጋጋሚ የተገነቡ መስመሮችን እያበላሹብን ይገኛሉ ሲሉም ተናግረዋል።

ስለዚህ መላው የከተማዋ ነዋሪ የመንገድ ዳር ፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ደህንነት እንዲረጋገጥ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲወጡ አሳስበዋል።

ዜና

# በመዲናዋ 31 ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች በውጭ ምንዛሪ እጥረት ወደ ሥራ አለመግባታቸው ተነገረ

## - 114 ኢንዱስትሪዎች በእሳት አደጋ ምክንያት ሥራ አቁመው እንደነበርም ተጠቁሟል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ 31 ከፍተኛ ኢንዱትሪዎች በውጭ ምንዛሪ እጥረት የተነሳ እስካሁን ወደ ሥራ እንዳልገቡ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ገለጸ። በበጀት ዓመቱ 114 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በእሳት አደጋ ምክንያት ሥራ አቁመው እንደነበረም ተነግሯል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝ ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ኃላፊ አቶ ኢዘዲን ሙስባህ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከተማ መስተዳድሩ በመዲናዋ ለሚገኙ ከ10 ሺህ በላይ ኢንዱስትሪዎች የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ነው። ሆኖም በከተማዋ የሚገኙ 31 ከፍተኛ ኢንዱትሪዎች በውጭ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት እስካሁን ወደ ሥራ አልገቡም።

በ2014 በጀት ዓመት የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ኤክስፖርት የማድረግ አቅም ለማሳደግ እና ተኪ ምርቶችን በብዛት እንዲያመርቱ ለማስቻል በትኩረት ሲሠራ ቆይቷል።

በበጀት ዓመቱ በሀገር አቀፍ ደረጃም ሆነ በአዲስ አበባ ደረጃ የአምራች ኢንዱትሪዎች የማምረት አቅም 50 በመቶ መሆኑንና ይህን ዝቅተኛ የማምረት አቅም ወደ 54 በመቶ ለማድረስ ሲሠራ ቆይቷል።

በግብዓት እና በውጭ ምንዛሬ እጥረት፤ የመሥሪያ ቦታ ችግርና በመሳሰሉት ምክንያቶች አምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም እምብዛም ሆኖ እንደቆየ የገለጹት አቶ ኢዘዲን፤ የማምረት አቅማቸውን ለማሳደግ ከተለያዩ ተቋማት ጋር በቅንጅት ሠርተናል ብለዋል።

እንደ አቶ ኢዘዲን ገለፃ፤ የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግ በርካታ ሥራዎችን በቅንጅት መሥራት ተችሏል። ከግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎች ጀምሮ የምንዛሬ ችግር ያለባቸውን በብሔራዊ ባንክ በኩል፤ የመሥሪያ ቦታ ችግር ያለባቸውን የመሥሪያ ቦታዎች አስተዳደርና ልማት ዘርፍ በኩል እንዲፈታ በማድረግ እንዲሁም የኃይል አቅርቦት ችግር ያለባቸውን በኤሌክትሪክ ሃይል በኩል እንዲፈታ በማድረግ ሰፊ እንቅስቃሴ ተደርጓል። በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ወደ 53 በመቶ ከፍ እንዲል ሆኗል ብለዋል አቶ ኢዘዲን።

ኃላፊው ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩ ኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም ለማሳደግና ቁጥራቸውን ከፍ ለማድረግም በትኩረት ሲሠራ ነበረ ብለዋል።

ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ውስጥ 568 ያህሉ ተኪ ምርቶችን እንዲያመርቱ ለማስቻል ዕቅድ ተይዞ ሲሠራ ነበር ያሉት አቶ ኢዘዲን፤ ከዕቅድ በላይ በሆነ አፈፃፀም 831 ኢንዱስትሪዎች ተኪ ምርቶችን እንዲያመርቱ በማስቻል በርካታ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ማዳን ተችሏል ሲሉ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ሕብረተሰቡን ማሳተፍ መቻሉ እና የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅም በመፈተሽ እንዲያድግ መደረጉ ለተገኘው ውጤት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማበርከታቸውን ተናግረዋል። አምራች ኢንዱስትሪዎች የድጋፍ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶ ድጋፍ እንዲያገኙ መደረጉም አጋዥ ነበር ሲሉም አክለዋል።

በሌላ በኩል በበጀት ዓመቱ ምርታቸውን ወደ ውጭ የሚልኩትን አምራች ኢንዱስትሪዎች ቁጥር ወደ 164 ከፍ ለማድረግ ታቅዶ ሲሠራ እንደነበር ገልጸው ሊሳካ የቻለው ግን 143 ያህሉ ብቻ እንደሆነ አብራርተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአጠቃላይ ወደ10 ሺህ 883 የአነስተኛ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች፣ መካከለኛ እና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ይገኛሉ ያሉት ኃላፊው፤ ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲያድጉ እና በዘርፉ መነቃቃት እንዲፈጠር በመንግሥት በኩል ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን አንስተዋል።

በ2014 በጀት ዓመት ግማሽ ቢሊዮን የሚጠጋ የብድር አቅርቦት እንዲቀርብላቸው መደረጉ ኢንዱስትሪዎች እንዲነቃቁ ማድረጉንም ተናግረዋል። 729 ኢንዱስትሪዎች ከልማት ባንክና ከአዲስ ካፒታል የማሽነሪ ሊዝ ኪራይ እንዲያገኙ መደረጉንም አንስተዋል። በበጀት ዓመቱ በኢንዱስትሪዎች ላይ በጥንቃቄ ጉድለት የሚፈጠር የእሳት አደጋ ፈታኝ እንደነበርም አቶ ኢዘዲን ተናግረዋል።



አቶ ኢዘዲን ሙስባህ

114 አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በእሳት አደጋ ምክንያት ሥራ አቁመው ነበረ ያሉት ኃላፊው፤ በኢንዱስትሪዎች የሚከሰቱ የእሳት አደጋዎችን ለመቅረፍ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የእሳት አደጋና ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በቅንጅት እየተሠራ መሆኑንና የእሳት አደጋዎችን መቀነስ መቻሉን ገልጸዋል።

# በጦርነቱ 68 ተንቀሳቃሽ እና 11 ቋሚ ቅርሶች ላይ ጉዳት መድረሱን ባለሥልጣኑ አስታወቀ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በሰሜኑ ጦርነት ወቅት በ68 ተንቀሳቃሽ እና 11 ቋሚ ቅርሶች ላይ ጉዳት መድረሱን የኢትዮጵያ ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለሥልጣን አስታወቀ። በጦርነት የወደሙ ቅርሶች ወደነበሩበት ደረጃ እንዲመለሱ ለማስቻል አስፈላጊው ጥገና በጊዜው እንዲደረግላቸው ሕብረተሰቡ በየአከባባው ለሚገኝ ጸጥታ አካል እና የቅርስ ጥበቃ ጽህፈት ቤት ጥቆማ በመስጠት የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያበረክትም ባሥልጣኑ አሳስቧል።

የኢትዮጵያ ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለሥልጣኑ በአሸባሪው ሕወሓት የጠፉ እና የወደሙ ቅርሶች በጊዜው ጥገና እንዲደረግላቸው እና ተመልሰው ወደነበሩበት ይዞታ እንዲመለሱ ለማስቻል በተካሄደው የዳሰሳ ጥናት 68 ተንቀሳቃሽ እና 11 ቋሚ ቅርሶች ላይ ጉዳት መድረሱን ማረጋገጥ ተችሏል።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ ወረራ በተካሄዳበቸው ቦታዎችና ነጻ በወጡ አካባቢዎች በተንቀሳቃሽ እና ቋሚ ቅርሶች ላይ የደረሱ አደጋዎችን በመቀነስ የጠፉትን ለማስመለስ በጥናት ላይ የተመሰረተ የመለየት ስራ ተሰርቷል። ሰሜን ጎንደር እና ሰቆጣ አካባቢ በጸጥታ ምክንያት ያልተዳረሱ ቦታዎች በመሆናቸው አደጋ የደረሰባቸው የቅርሶች ቁጥር ሊጨምር እንደሚችልም ገልጸዋል።

ባለሥልጣኑ ለደረሱት ጉዳቶች መፍትሄ ለመስጠት ሁለት አቅጣጫዎችን አስቀምጦ እየሰራበት ይገኛል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ ሙዚየም ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩ ፣ቤተ እምነቶች አብያተ ክርትያናት እና መዝጊዶች ጉዳት የደረሰባቸው ቅርሶች በጥቋሚነት ጥገና እስከሚደረግላቸው ድረስ ወዲያውኑ ፈጣን ጥገና ተደርጎላቸው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ በሚያደርጉ ስራዎች ላይ ትኩረት በማድረግ እየተሰራበት ነው። ኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታው ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ መልሶ ለመቋቋም 159ሺህ ዶላር ከዓለም ባንክ በቀረበሳ ጥያቄ መሰረት ተግባራዊ የማድረግ ስራዎች በቀጣይነት እንየተሰሩበት ሆኑን ገልጸዋል።

ከቅርስ ጋር የሚሰሩ የተዘረፉ ተቋማትን እንደገና የማጠናከር ስራዎች የባለሽልጣኑ ቀጣይ ስራ መሆኑን ጠቅሰሳ ከጉዳቱ አንጻር ለየትኛው ቅድሚያ ጥገናና እና ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል የሚለው በጥናት ምላሽ ይሰጥበታል ብለዋል።

ተቋማቱ ከደረሰባቸው ጉዳት የተነሳ ከላሊበላ ጀምሮ የእለት ከእለት ስራቸውን ለመስራት የሚያዳግታቸው ደረጃ ላይ የደረሱ ቅርሶች እንዳሉም አያይዘው ገልጸዋል።

ፎቶ - ከፋይል



ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው

ባለሥልጣኑ የጠፉትን ቅርሶች ለማስመለስ ከጉምሩክ እና ከፀጥታ አካላት ጋር እየሰራ መሆኑን አስታውሰው አንድ ቅርስ ከቦታው ተሰረቀ ማለት አንድ አካል መውሰዱን ስለሚያሳይ በሚቻል መንገድ ሁሉ በፖሊስ ትብብር እና ክትትል ተደርጎ የማስመለስ ስራው እንደሚቀጥል ገልጸዋል። ካልሆነ ግን ከሀገር እንዳይወጣ ለማድረግ ከጉሙሩክ ጋር አስፈላጊው ስራ እየተሰራበት ነው ብለዋል።

ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ አንዳንድ ቅርሶች እንደጠፉ የሚነገርበት ሁኔታ እንዳለ የጠቆሙት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ነገር ግን የጠፋው ቅርስ ካታሎግና መለያ ቁጥር እስካለው ድረስ የትም ሀገር ይሂድ የኢትዮጵያ ንብረት በመሆኑ ሊታወቅ እንደሚችል ጠቅሰዋል።

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው ገለጻ፤ የቅርስ ዋጋ መገመት አይቻልም ፣ የወደሙ ቅርሶችን ለመጠገን የሚያስፈልገውን ወጪ ለመገመት ያልተዳሰሱ ቦታዎች ከተዳሰሱ በኋላ አስፈላጊው ጥናት ተካሂዶ በቁጥር ይገለጻል።

በአሁኑ ወቅት ለቅርሶች ልማት ትልቅ ትኩረት በተሰጠው መሰረት ባለሥልጣኑ አዳዲስ ቅርሶች በኢኮኖሚ ውስጥ እንዲገቡ ለማድረግ ከክልሎች ጋር ቅርሶችን የማልማት ስራዎች እየሰራ መሆኑን የጠቀሱት ረዳት ፕሮፌሰር አበባው፤ በጅማ ፣ሀረር፣ ድሬዳዋ ኦሮሚያ ክልል እና አማራ ክልል ከላሊበላ ጋር የሚሰሩ ዘርፈ ብዙ ስራዎችና በዕድቅ ደረጃ የተያዙ ስራዎችን ለአብነት አንስተዋል።

በጦርነት የተጎዱ ቅርሶች አካባቢ የሚኖር ሕብረተሰብ ክፍል ስለማንኛውም ቅርስ ያለውን መረጃ ሁሉ ለፖሊስ እና በአከባቢያቸው ለሚገኝ ቅርስ ጽህፈት ቤት በማቀበል በቅርስ ማዳን እና ማስመለስ ስራ የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ ኃላፊው ጥሪ አቅርበዋል።

# እየተወሰደ ባለው የተቀናጀ እርምጃ በዞኑ የሚገኘው የሽብር ቡድን እየተዳከመ መምጣቱ ተነገረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በቄለም ወለጋ ዞን በሚገኘው የሽብር ቡድን ላይ እየተወሰደ ባለው የተቀናጀ እርምጃ ቡድኑ እየተዳከመ መምጣቱ ተነገረ።

በቄለም ወለጋ ዞን ዋና አስተዳዳሪ አቶ ገመቹ ጉርሜሳ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት በሀገር መከላከያ ሰራዊት፣ በፌዴራል ፖሊስ፣ በክልሉ ልዩ ኃይልና በሌሎች በአካባቢው የሚገኙ የፀጥታ አካላት አማካኝነት በአሸባሪው የሸኔ ቡድን ላይ እየተወሰደ ባለው ቅንጅታዊ እርምጃ ቡድኑ እየተዳከመ መጥቷል።

በቅርቡ በተለይም በቄለም ወለጋ ሀዋ ገላን ወረዳ ላይ ያነጣጠረው ከፍተኛ ብሔር ተኮር ጥቃት የፀጥታ አካላቱ አማካኝነት ሊደርስ የነበረው ከፍተኛ ጉዳት ሊከሽፍ መቻሉን አውስተው፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ በሺዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው ማሕበረሰብ መፈናቀላቸውን ተናግረዋል።

የተፈናቀሉ የማሕበረሰብ ክፍሎችን የዞኑ መስተዳድር ከክልሉ ቡሳ ጎኖፋና ከመላው የአካባቢው ማሕበረሰብ ጋር በመተባበር የተፈናቀሉ ወገኖችን ወደ ቀያቸው የመመለስና መልሶ የማቋቋም ተግባር ሲከናወን መቆየቱን ገልጸዋል።

በተጨማሪም በሽብር ቡድኑ ምክንያት የወደሙና የተዘረፉ ሀብቶችን በመንግሥትና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት እንዲሁም ከአካባቢው ማሕበረሰብ ጋር በመሆን የማቋቋም ስራዎች እንደተከናወኑ አስታውቀዋል።

መንግሥት ይህን የሽብር ቡድን ከስር መሰረቱ ለማጥፋት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ እንደሚገኝ ያነሱት ዋና አስተዳዳሪው የሽብር ቡድኑን አረመኔያዊ ተግባር በማውገዝም ሆነ በመታገል ረገድ የአካባቢው ማሕበረሰብ ከጫፍ እስከ ጫፍ ከፀጥታ አካላት ጋር ሆኖ እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

በዚህም በአሁኑ ወቅት ጠላት በከፍተኛ ሁኔታ እየተመታ በመምጣቱ ምክንያት ከመንግሥት የፀጥታ ኃይል ፊት መቆም የተሳነው በመሆኑ በየደረሰበትና በየሸሸበት ስፍራ በንፁሐንና በሌሎች ብሔሮች ላይ ያነጣጠረ የበቀል ተግባር ላይ መሰማራቱን አብራርተዋል።

የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ የመንግሥት ዋነኛ ኃላፊነት በመሆኑ ማሕበረሰቡ ወደ አካባቢው እንዲመለስ በሚደረግበት ወቅት የደህንነት ስጋት እንዳይገባው የፌዴራል መንግሥቱና የክልሉ የፀጥታ አካላት በአካባቢው ተመድበው እየሰሩ እንደሚገኙ ገልጸዋል።



አቶ ገመቹ ጉርሜሳ

ጠላት ይገኝበታል ተብሎ በሚገመቱ አካባቢዎች መንግሥት በሚወስደው እርምጃና ኦፕሬሽኖች ጠላት በመሸሽና በሌሎች አካባቢዎች ሾልኮ በመግባት በንፁኃን ዜጎች ላይ ጥቃት የማድረስ ተግባር ላይ ተሰማርቷል ብለዋል።

የጠላትን ኃይል ለማዳከም ብሎም ለማጥፋት በሁለት መልኩ እየተሰራ እንደሆነ የተናገሩት ዋና አስተዳዳሪው፣ በአንድ በኩል የፌዴራል፣ ክልልና የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት ጠላት ይገኛል ተብሎ በሚገመትበት አካባቢዎች ሁሉ በማጥራት የጠላትን ኃይል በመደምሰስ ሌላው ደግሞ እጅ እንዲሰጥና እንዲማረክ ተደርጓል ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በአካባቢው ሚሊሻ፣ ልዩ ልዩ የማሕበረሰቡ አደረጃጀቶች አማካኝነት ፖለቲካዊ ኦፕሬሽን በማከናወን ማሕበረሰቡ ጠላትን ፊትለፊት እንዲፋለም፣ መረጃዎችን እንዲሰጥና ባለማወቅ በሽብር ቡድኑ ውስጥ የተቀላቀሉ ልጆቹን እንዲመልሱ የማድረግ ስራ በሰፊው እየተሰራ ይገኛል።

አመራሮች እጃቸው አለበት ተብሎ የሚናፈሰው አሉባልታ ተጨባጭ አይደለም ያሉት አስተዳዳሪዎቹ፣ ለዚህም ማሳያ የሚሆነው ደግሞ በደምቢዶሎ ብቻ 148 የፖለቲካ አመራሮች መሰዋታቸው ፣ ከዚህም ባለፈ የማህበረሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ የተሰማሩ በርካታ የፀጥታ አካላት የሕይወት መስዋዕትነት እየከፈሉ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

# “አትሌቶቻችን በጠንካራ የቡድን መንፈስ የተጎናጸፉትን ድል በሌሎችም መስኮች መድገም ያስፈልጋል”

## - አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ

**ዳግማዊት ግርማ**



ፎቶ - ከፋይል

አዲስ አበባ፡- አትሌቶቻችን በጠንካራ የቡድን መንፈስ የተጎናጸፉትን ድል በሌሎችም መስኮች መድገም ያስፈልጋል ሲል አትሌት ሻለቃ ኃይሌ ገብረስላሴ ተናገረ፡፡

አትሌት ኃይሌ በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ በተጎናጸፈችው ድል የተሰማውን ደስታ በመለግጽ ለመላው ሀገሪቱ ዜጎችም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክቱን አስተላልፏል፡፡

አትሌቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ ጠንካራ የቡድን ስሜት በታየበት የኦሪገኑ ዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይ ያመጡትን ድል በሌሎችም መስኮች መድገም ያስፈልጋል፡፡

የአትሌቶቹ ድል የተገኘው ኢትዮጵያን በማስቀደማቸውና ከሰፈር አስተሳሰብ ወጥተው ሀገራቸው በኃያላኑ ሀገራት ፊት ደምቃ እንድትታይ ባደረጉት ጥረት መሆኑን የጠቆመው አትሌት ሻለቃ ኃይሌ፤ የአትሌቶቹ አኩሪ ተግባር በሌሎቹም ዘርፎች ላይ መደገም እንዳለበት ጠቁሟል፡፡

አትሌቶቹ ችግሮቻቸውን ሳያስቡ ሀገርን በማስቀደም ያመጡት አኩሪ ድል የሚያስመሰግናቸው መሆኑን የገለጸው አትሌት ኃይሌ፤ ማሕበረሰቡም ሰከን ብሎ በማሰብ ወደ አንድ የሚያመጣው ጉዳይ ላይ ትኩረት በመስጠት መስራት እንደሚገባው ተናግሯል፡፡

አትሌቶቹ በዓለም አቀፍ ደረጃ ላስመዘገቡት ድል ምስጋናውን ያቀረበው አትሌት ኃይሌ፤ አትሌቶቹ በነበራቸው የቡድን ስራ እንዲሁም ሀገራዊ ስሜት ምክንያት ኢትዮጵያ በተጎናጸፈችው ድል የተሰማውን ደስታ በመለግጽ ለመላው ሀገሪቱ ዜጎችም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክቱን አስተላልፏል፡፡

ኢትዮጵያ በቅርቡ ሁሉም ሊኖርባትና ኢትዮጵያዊ ሆኖ መፈጠር የሚያስቀናበት ጊዜ ላይ እንደምንደርስ አምናለሁ ያለው አትሌት ኃይሌ ያችን ሀገር ለመፍጠር ሁሉም ሊረባረብ እንደሚገባውም ገልጿል፡፡

“የዘንድሮ ሩጫ ከሩጫ በላይ ነው፤ ከውጤቱም በላይ ሀገራዊ ጉዳይ የቀደመበት ሰንደቋም በክብር የተውለበለበበት” ነው ያለው አትሌት ኃይሌ፤ የኢትዮጵያና ልጆቿ የከፍታ ጣርያ የተስተዋለበት መሆኑን በመግለጽ ኢትዮጵያውያንን በብዙ ያስተማረ እንደነበርም ተናግሯል፡፡

ከሁለት መቶ በላይ ሀገራት በተሳተፉበት ውድድር ላይ በሁለተኝነት ማጠናቀቋና የአትሌቶቹም ኢትዮጵያዊ አብሮነት በመላው ዓለም ላይ ኢትዮጵያን በበጎ ጎን ማስተዋወቅ መቻሉን የተናገረው አትሌት ኃይሌ፤ በሌሎች መልካም ነገሮችም በዓለም ፊት መታወቅ የምትችልበትን መንገድ ማመቻቸት እንደሚገባም ጠቁሟል፡፡

ከትግራይ አካባቢ የመጡት አትሌቶች በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት ወላጆቻቸውን ማየትና ማግኘት በማያስችል ችግር ውስጥ ሆነው እንኳን ሀገርን በማስቀደም የሀገራቸውን ሰንደቅ ከፍ ማድረጋቸው የሚያስመሰግናቸው መሆኑን የገለጸው አትሌት ኃይሌ፤ ማሕበረሰቡም የአትሌቶቹን መንገድ በመከተል ችግርን ወደ ጠረጴዛ ዙሪያ የማምጣትን ባህል ማዳበር እንደሚያስፈልግ ገልጿል፡፡

በአሜሪካ ኦሪገን በተካሄደው 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ አራት የወርቅ፣ አራት የብር እንዲሁም ሁለት የነሀስ በድምሩ አስር ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ውድድሯን ከአፍሪካ አንደኛ፣ ከዓለም ሁለተኛ ሆና ማጠናቀቋ ይታወቃል፡፡

# የኢትዮጵያዊነት ጥግ በዓለም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኗ ትንግርት የሚሆንባቸው ጥቂቶች አይደሉም።

እንቁ አትሌቶቿም በተለይም ባለፈው የቶኪዮ 2020 ኦሊምፒክ የተለመደ ድል ደራርበው ባለመታየታቸው በአትሌቲክስ ያላቸው ገናና ስም እንዳበቃለት ብዙዎች ያስቡ ነበር። ወርቃማ አትሌቶችን ሁሌም ማፍራት የማይነጥፍበት የኢትዮጵያ ማሕጸን ግን ዛሬም በብዙ ችግሮች ውስጥ አልፎም ስሟን የሚያስጠሩ እንቁዎችን ከመውለድ ወደ ኋላ አላለም።

ኢትዮጵያ ልትበተን ቋፍ ላይ ደርሳለች፣ ኢትዮጵያዊነትም እንደጉም የሚበንንበት ቀን ሩቅ አይደለም ሲባል ኦሪገን ላይ ይባስ ጎምርቶ ታይቷል። ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም የሉም ሲባሉ ይበልጥ በተደራራቢ ድሎች አንጸባርቀው መጥተዋል። ኢትዮጵያ እንዲህ በአራቱም አቅጣጫ ውጥረት ውስጥ ባለችበት ሁኔታ ከዚህ ቀደም በአትሌቲክስ የስኬት ታሪኳ አይታ የማታውቀውን ድል በማይበገሩት ጀግኖች አትሌቶቿ ተጎናጽፋለች። በታሪኳ ከፍተኛውን ሜዳሊያ በማግኘትም ሃያሏን አገር አሜሪካን ተከትላ ከዓለም ሁለተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ቀዳሚውን ደረጃ ይዛ አጠናቃለች።

በወንዶች እና ሴቶች ማራቶን እንዲሁም በ10ሺ እና 5 ሺ ሜትር ሴቶች 4 ወርቅ፣ በ3ሺ ሜትር መሰናክል በሴት እና ወንድ እንዲሁም በወንዶች ማራቶን እና በ 1500 ሜትር ሴቶች የብር ሜዳሊያ፣ በሴቶች 3 ሺ መሰናክል እና በ5 ሺ ሜትር ሁለት የነሐስ ሜዳሊያዎች ኢትዮጵያን የስኬት ማማ ላይ አስቀምጠዋታል። ኢትዮጵያውያን ከስፖርት ስኬት በዘለለ ትርጉም ባለው ቻምፒዮና እንቁዎቹ አትሌቶቿ ውድ አገራቸውን በሜዳሊያ ብዛት ብቻ አላጥለቀለቁም። በየውድድሩ ከተገኙት ድሎች ጀርባ የኢትዮጵያውያን አልሸነፍ ባይነት ዛሬም እንደ ጥንቱ እንዳልተለያቸው ታይቷል። ኢትዮጵያውያን ተለያይተዋል ሲባል አንድ ላይ አብረው አገራቸውን እንደሚያስጠሩ አስመስክረዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ከሜዳሊያዎቹ መመዝገብ በላይ የከዋከበት አትሌቶቹ የአንድነት መንፈስ፣ አልሸነፍ ባይነትና መስዋትነት ይበልጥ የደስታው ምንጭ ሆኗል። ከራስ በላይ አገርን፣ የግል ስኬትን ወደ ኋላ ብሎ ለሰንደቅ ዓላማ ክብር መቆምን በብርቅየዋ ቻምፒዮን ለተሰንበት ግደይ የ5 ሺ ሜትር ውድድር አስተውሎታል። በሌላው ማሸነፍ ውስጥ ራስን መስዋት አድርጎ አገር በወርቅ ስታጌጥ ከልብ በመነጨ ደስታ መሳቅን ሁሌም የኢትዮጵያ የኩራት ምንጮች የሆኑት ጀግኖች አሳይተዋል። ራስን ዝቅ አድርጎ የአገርን አንገት ቀና ማድረግ ያለውን ስሜት ለዓለም ጭምር አስተምረዋል። የኢትዮጵያዊነት ጥግ የት ድረስ እንደሚዘልቅ በዓለም አደባባይ በገሃድ አውጥተዋል።

የጀግኖቹ ስኬት ጀርባ የምትገኘው ፍልቅልቋ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኮማደር ደራርቱ ቱሉ በኦሪገን የታየው የኢትዮጵያዊነት ጥግ የተገለጸባት የአገር ኩራት መሆኗን የልጆቿን ጫማ ዝቅ ብላ በማሰርና በእያንዳንዱ ድል የደስታ እንባ በማፍሰስ በተግባር አሳይታለች። ልዩነትን ሳይሆን አንድነትን በገሃድ አውጥታ ዛሬም የአገር ምልክት መሆኗን አስመስክራለች። በአትሌቲክስ የውድድር ዘመኗ ድል አድርጋ በዓለም አደባባይ ከፍ ያደረገችውን ሰንደቅዓላማም በአንድ ወቅት እንዲህ ስትል ገልፃው ነበር ‹‹ስለኢትዮጵያ ባንዲራ መናገር አልችም፣ አቅምም የለኝም ፤ ኢትዮጵያ የሚለው የስፖርት ቱታ የክብር ልብሴ ነው፣ እኛ አገር ሕዝቡ ተመችቶት አልያም ደልቶት አይደለም የሚኖረው፣ አገሩን ከነ ችግሩ ስለሚወዳት ነው››።

ደራርቱ ቱሉ ዛሬም በኦሪገን ከጣፋጩ ድል በኋላ ትናገራለች ‹‹ኢትዮጵያ ሁሌም በልጆቿ ትከበር፣ ትሳቅ፣ ትደሰት። በአሜሪካ ኦሪጎን 2020 ዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለተገኘው ታሪካዊ ውጤት እንኳን ደስ አለን። አገራችንም እንኳን ባንዲራዋ በዓለም አደባባይ ከፍ ብሎ ተውለበለበ፤ ኢትዮጵያ ደግማ ደጋግማ ከፍ ትበል። ይህ ድል የአዲስ ዓመት ገጸበረከት ነው። መጪው አዲስ ዓመት በየቦታው የሚሰማው መጥፎ ነገር ተወግዶ ተባብረን አገራችንን ወደፊት የምናስኬድበት ይሁንልን››።

ደራርቱ በእሷ የአመራር ዘመን በመጣው ታላቅ ውጤት ተኩራርታ አትቀመጥም። ነገም አገሯን ለማኩራት ዝግጁ ናት። ‹‹የተሻለ ውጤት በመምጣቱ ልንዘናጋ አይገባም፤ ምክንያቱም የዛሬ ዓመት ቡዳፔስት ላይ የዓለም ቻምፒዮና ከሁለት ዓመት በኋላ ደግሞ ፓሪስ ላይ ኦሊምፒክ አለ። ሁሌም በአንድነት፣ በመደጋገፍና በመስማማት ከተጋን ውጤታችንን እናስጠብቃለን›› ስትል ከኦሪገን መልዕክቷን አስተላልፋለች።





የአማራ ክልል ምክር ቤት መደበኛ ጉባዔ

# “በውስጥና በውጭ የገጠመንን ፈተና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዶክተር ይልቃል፤ ትህነግ ታሪክ ይቅር የማይለው በደል በአማራ ክልል ማድረሱንም አስታውሰዋል።

የትህነግን ወረራ መቀልበስ ቢቻልም አሁንም ነፃ ያልወጡ የክልሉ አካባቢዎች መኖራቸውን እና ከወረራ ነፃ የወጡ አካባቢዎችን በማረጋጋትና መልሶ በመገንባት በኩል ስኬታማ ሥራ መሠራቱንም አስታውቀዋል።

የወደሙ ንብረቶች ከነበረው በበለጠ እንዲገነቡ ይደረጋል ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ በክልሉ የነበሩ ሕገ ወጥ እንቅስቃሴዎችን ማስቆም እንደሚገባ ከሕዝብ በተነሱ ጥያቄዎች መሠረት የሕግ ማስከበር ሥራ መሠራቱንም አስታውቀዋል።

ከሱዳን ድንበር ጋር የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ከፌዴራል መንግሥት ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

እንደ ዶክተር ይልቃል ገለጻ፤ ከአጎራባች ክልሎች ጋር መልካም ግንኙነትን ለማጠናከር እየተሠራ ነው። በተለይ ከአፋርና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ጋር ያለው ግንኙነት ተቋማዊ ቅርጽ እየያዘ ውጤት እያስመዘገበ ይገኛል፡፡ የጦር መሣሪያ አያያዝንና አጠቃቀምን ሕጋዊ ለማድረግም እየሰተራ ነው፡፡

እንደ ሀገር ተጋርጦ የነበረውን አደጋ ለመቀልበስ በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን የተናገሩት ርእሰ መስተዳድሩ፤ አሁንም ማንነትን መሠረት ያደረጉ ግድያዎች መፈናቀሎች የተረጋጋ አካባቢ እንዳይኖር የማድረግ አጥፊ ተግባራት እየተፈጸሙ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በክልሉ የተጀመረውን ሕግ የማስከበር ሥራ ከሕዝብ ጋር ሆነን አጠናክረን እንቀጥላለን ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ ከክልሉ ውጭ የሚፈጸሙ ማንነት ተኮር ጥቃቶችን ለመታደግ ከፌዴራል እና ከክልል መንግሥታት ጋር በጋራ እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል። ሕዝቡ በአንድነት እና በጋራ እንዲቆምም ጥሪ አቅርበዋል።

ርእሰ መስተዳድሩ በአማራ ክልል በሚቀጥሉት ዓመታት የግብርና ምርታማነትን በእጥፍ ለመጨመር እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል። በ2014/15 የምርት ዘመን 4 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በማረስ 143 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት መታቀዱንም አስታውሰዋል። በዚህም እስካሁን 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታሩ መታረሱን ገልጸዋል።

ተከታታይ አራት ዓመታት የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሃግብር ተግባራዊ ለማድረግ በበጀት ዓመቱ 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን በማፍላት እየተተከሉ መሆኑን የተናሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ በአንድ ጀንበር ተከላ 250 ሚሊዮን ችግኞችን የመትከልና ሌሎች ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነም ጠቁመዋል።

በበጀት ዓመቱ የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት፣ የሥጋ፣ የወተት፣ የእንቁላል፣ የማር ምርት እና ሌሎችንም ተያያዥ ምርቶች ወደ ገበያ በማቅረብ በኩል የተሻሉ አፈጻጸም መመዝገቡን አመላክተዋል።

ዶክተር ይልቃል፤ ለገጠር ኢንቨስትመንት አገልግሎት የሚውል መሬት ልየታና አቅርቦት ሥራዎችን በማከናወን በበጀት ዓመቱ 11 ሺህ 881 በላይ ሄክታር መሬት የመለየት ሥራ ተሠርቷል ብለዋል። የ801 ባለሀብቶች የልማት አፈጻጸም በመገምገም 62 ነጥብ 8 በመቶ ለሚሆኑት ባለሀብቶች የልማት አፈጻጸም ፕሮፋይል መሞላቱንም ተናግረዋል።

ዶክተር ይልቃል ዘመናዊ፣ ፍትሐዊና በውድድር ላይ የተመሠረተ የንግድ ሥርዓትን በማጠናከር በንግድና ገበያ ሥርዓት ላይ ተመስርቶ የሚሠራ የንግድ ማሕበረሰብ እና ሸማችን የመፍጠር ሥራ በእቅድ ተይዞ እየተከናወነ ይገኛል ነው ያሉት።

ጉባኤውን በንግግር የከፈቱት የምክር ቤቱ ዋና አፈ ጉባኤ ወይዘሮ ፋንቱ ተስፋዬ በበኩላቸው ጠላት በአማራ ሕዝብ ላይ በሚያራምደው የተሳሳተ ትርክት ምክንያት በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የአማራ ሕዝብ ዋጋ እንዲከፍል እያደረገው ነው ብለዋል።

የአማራ ሕዝብ ለሀገሩ ቀናኢና በሕግና ሥርዓት የሚያምን በመሆኑ አሁን እየደረሱ ያሉ ችግሮችን ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በመሆን ይሻገራቸዋልም ብለዋል።

በሌላ በኩል መንግሥት በክልሉ ያከናወነው የሕግ ማስከበር ስራ የሕዝቡን ጥያቄ የመለሰ መሆኑንም አንስተዋል።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአማራ ሕዝብ ላይ ወረራ በመፈጸም ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳት ማድረሱን የተናገሩት ዋና አፈጉባኤዋ፤ አሁንም የህልውና ዘመቻው ሙሉ ለሙሉ እንዲጠናቀቅ መስራት ያስፈልጋልም ብለዋል።

በጥቃት ከቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም እየተከናወኑ ያሉ ተግባራትም ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ ዋና አፈ ጉባኤዋ ገልጸዋል። “አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በከፈተው ጦርነት በክልሉ ሕዝብ ላይ በርካታ ሰብዓዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ እና ቁሳዊ ጉዳቶች ደርሰዋል” ሲሉ አስታውሰዋል።

የአማራ ክልል መንግሥት በጦርነቱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች ለመደገፍ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር አስፈላጊውን ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ በቀጣይም ድጋፉ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

መንግሥት ችግሩ በሰላማዊ መንገድ እልባት እንዲያገኝ አሁን እየተከተለ ያለውን የሰላም አማራጭ የአማራ ክልል ምክር ቤት እንደሚደግፍም ገልጸዋል።

ግጭት የሚፈታው በጦርነት ብቻ እንዳልሆነ የክልሉ ምክር ቤት እንደሚያምን አመልክተው፤ “የሰላም አማራጩ የኢትዮጵያን ጥቅምና ሉዓላዊነት የሚያስከብር እንዲሆን የበኩላችንን አስተዋጽኦ ለማድረግ ዝግጁ ነን” ብለዋል።

የሰላም አማራጭ በአንድ ወገን ፍላጎት ብቻ የሚሳካ እንዳልሆነ ገልጸው፤ አሁንም በድንበር አካባቢ ተጨባጭ ትንኮሳዎች እየታዩ በመሆኑ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የክልሉ መንግሥት የህልውና ዘመቻው በስኬት እንዲጠናቀቅና ሕግ ማስከበር ላይ በትኩረት ሲሰራ እንደነበር ያስታወሱት አፈ ጉባኤዋ በተጠና መንገድ በተከናወነው ሕግ የማስከበር ስራ ዜጎች ሰላም ማግኘታቸውን ተናግረዋል።

በቀጣይም የሕግ ማስከበር ስራው ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሕብረተሰቡ ፍላጎት መሆኑን አመልክተዋል።

ምክር ቤቱ ለአራት ቀናት በሚያካሂደው ጉባኤ የሥራ አስፈጻሚ አካላት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የንጋት ኮርፖሬት የ2014 በጀት ዓመት የሥራ አፈጻጸም ሪፖርቶችን ይገመግማል እንዲሁም፤ የተለያዩ አዋጆችንና ሹመቶችን ያጸድቃል ተብሎ ይጠበቃል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ኢትዮጵያ በልጆቿ አሸንፋ ዛሬም የአፍሪካ ኩራትና ድምቀት ሆናለች!

ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ትናንትም፣ ዛሬም ከአሸናፊነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ሆነው ዘልቀዋል። ኢትዮጵያ ስትነሳ ነጻነትና ያልተደፈረ ሉዓላዊነቷ፤ ኢትዮጵያዊነት ሲወሳም የአልበገር ባይነት፣ የጽናት እና የአሸናፊነት ተምሳሌትነት ሕያው ሓውልት ሆኖ ይናገራል። ይህ የአሸናፊነትና የአልበገር ባይነት ተምሳሌትነት ደግሞ በአንድ መስክና ገጽ ብቻ የሚነበብና የሚገለጽ አይደለም። ይልቁንም ከኪነጥበብና ኪነ ሕንጻ ከፍ ያለ አሻራቸው ጀምሮ በጦር አውድማ፣ በስፖርት በተለይም በአትሌቲክሱ መድረክ እጅጉን የደመቀ ሆኖ እንጂ።

በዘርፈ ብዙ ገጻቸው ከፍ ብለው በዓለም አደባባይ ተምሳሌትነታቸው ለአፍሪካ ኩራትም፣ ድምቀትም ሆነው የሚገለጹት ኢትዮጵያውያን፤ ኢትዮጵያዊነትን ሲያደምቁ፣ ኢትዮጵያን ሲያኮሩ፣ ለአፍሪካ ከፍታ ሲታትሩ ትናንትን አሳልፈዋል። ዛሬንም በዚሁ ከፍታ ዘልቀው ተገልጠዋል። የራሷን ፊደል ቀርጻ እና ዘመንን ቀምራ የራሷን ከፍታ ያሳየች፤ ለአፍሪካም መጠሪያ የሆነችው ኢትዮጵያ፤ በዓድዋ ተራሮች የነጻነትና የአልደፈር ባይነትን ችቦ ለኩሳ ከአፍሪካም አልፋ ለመላው ጭቁኖች ብርሃን አቀብላለች። በብርሃኗ ተመርተውም አፍሪካውያን በድል አድራጊነት እንዲደምቁ፤ በነጻነት ቀና ብለው እንዲራመዱ አርዓያም ሆናለች።

ይህ እንደ አብሪ ኮከብ አብርቶ፣ አፍሪካን የማድመቅ ጉዞ በዚህ አልተገታም። ይልቁንም አፍሪካ የአሸናፊነት ቀርቶ የተሳትፎ ታሪኳ እምብዛም ባልሆነባቸው ዘመናት የስፖርት በተለይም የአትሌቲክሱ መድረክ ሌላ ታሪክን መጻፍ ቻለች። በሮም አደባባይ በአበበ ቢቂላ የተጀመረው የኢትዮጵያም፣ የአፍሪካም የአሸናፊነት ጉዞ፤ በአትሌት ደራርቱ ቱሉ ባርሴሎና ላይ በአፍሪካ መድረክ የሴቶችን ከፍ ያለ የድል መንገድ አደላድሎ አቀበለ። ይሄም ኢትዮጵያውያን እንደ ሕዝብ፣ ኢትዮጵያ ደግሞ እንደ አገር ለአፍሪካ የድል ብስራት ፈር ቀዳጅነታቸው፣ የመንገዳቸው ብርሃን ፈንጣቂና የአፍሪካውያን ድምቀት መሆናቸውን በስፖርቱም መድረክ እንዲያረጋግጡ አድርጓቸዋል።

ይህ የኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያውያን ከራስ ያለፈ የአፍሪካ ኩራትና ድምቀትነት እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም የቀጠለ ሕያው ጅረት ሆኗል። የነጻነቱን አብነት ቀጥለው በልማቱም መስከ አፍሪካ በራሷ አቅም ምንም ማድረግ እንደምትችል ያረጋገጡበትን የታላቁን የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ እውን አድርገው አሳይተዋል። የኒዮኮሎኒያሊዝም እሳቤ ያሰከረው የዲፐሎማሲ ጫናና እጅ ጥምዘዛ ሊያንገዳግዳቸው እንደማይችልም በ"ኖ ሞር" ንቅናቄ የውስጥ ኃይልን አስተባብሮ አፍሪካውያንን በአንድ አሰልፎ ታሪክ በመጻፍ ተረጋገጠ። ኢትዮጵያም፣ ከውጪ ጠላቶች፣ ከውስጥ ተላላኪ ባንዳዎች አንድነቷን ንደው ሊያዳክሟት ሲጥሩ፤ በሕብር የደመቀ አንድነቷን የበለጠ በማጋመድ አሸንፋ ወጥታ የድል ጉዞዋን ገልጣለች።

ይህ ብቻም አይደለም፤ ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው በውስጥ መቀጠል፤ በዓለም መድረክም መገለጥ አይችሉም በሚባልበት በዚህ ወቅት፤ ኢትዮጵያውያን የበለጠ አንድ ሆነውና ተናብበው ሌላ አዲስና ደማቅ ታሪክን ለራሳቸውም ለአፍሪካም መጻፍ ችለዋል። 18ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ደግሞ የዚህ ሕያው ምስክር ሆኖ በታሪክ ድርሳን ለመከተብ በቅቷል። ይህ መድረክ ደግሞ የራሱ ልዩ ባህሪ አለው። ምክንያቱም የኢትዮጵያን አሸናፊነት ያበሰሩ፤ ለአፍሪካም ድምቀት የሆኑ አትሌቶች የኦሪገን ጉዞ የተመራው፤ ትናንት በኦሎምፒክ መድረክ ኢትዮጵያንም፣ አፍሪካንም ማሸነፍ የሚችሉ ሴቶች እንዳሏቸው በአትሌቲክስ ተሳትፎዋ ወርቅ አምጥታ በዓለም አገሯንም ኢትዮጵያንም ባደመቀችው አትሌት ደራርቱ ቱሉ መሪነት መሆኑ ነው።

እርግጥ ነው፣ አሸናፊነትን የሚያውቅ ለማሸነፍ ቅርብ ነው፤ ለማሸነፍ ቅርብ የሆነ ደግሞ አሸናፊዎችን የመፍጠር አቅሙ ከፍ ያለ ነው፤ አሸናፊዎች ሲፈጠሩ ደግሞ አገር እንድታሸንፍ የሚያስችል የሕብረትና የጽናት ኃይል ገዝፎ ይገለጣል፤ ይህ ሲሆን አገር በልጆቿ ታሸንፋለች፤ ታሪክ ራሱን እየደገመ አገር ከፍ ብላ ለአህጉር ድምቀትን ትቸራለች። በዚህ የዓለም ሻምፒዮናም የሆነውም ይሄው ነው። ኢትዮጵያዊነት የገባቸው፤ አሸናፊነት የናፈቃቸው ብርቱ የኢትዮጵያ ልጆች ኦሪገን ላይ ተገኙ፤ በጽናት ተወዳድረው በላባቸው አሸናፊነትን ተጎናጸፉ፤ ኢትዮጵያን ከድል ሰገነት ላይ አኖሩ። ኢትዮጵያም በልጆቿ ከማሸነፍም በላይ ሆነች።

ይህ የኢትዮጵያ የድል ሰገነት ደግሞ በአትሌቲክስ ሻምፒዮና ታሪክ የራሱን አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ሆነ። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት በታሪኳ አስር (አራት የወርቅ፣ አራት የብር፣ ሁለት የነሃስ) ሜዳልያዎችን በመሰብሰብ፤ ከአዘጋጇ አሜሪካ ቀጥሎ በዓለም ሁለተኛ፣ በአፍሪካ ደግሞ አንደኛ ደረጃን ይዛ ውድድሩን እንድታጠናቅቅ አደረጋት። እናም ኢትዮጵያ በልጆቿ አሸንፋ ከፍ ስትል፤ እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም በዓለም አደባባይ ለአፍሪካውያን ኩራት፤ ለአህጉሯም ድምቀት ሆነች። ይቻላልን ትናንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም በዓለም መድረክ ችላ አሳየች። መተባበርና በጋራ መቆም የተገዳዳሪዎችን ወጥመድ በጣጥሶ መውጣት የሚያስችል ኃይል መሆኑን አረጋገጠች። እናም ኢትዮጵያ አሸንፋ የማሸነፍን ብርሃን ዳግም ለዓለም አሳየች፤ አፍሪካንም አኮራች!


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሀሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

# ክረምቱ የሰው አዝመራ የምናፈራበት ይሁን

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

በአገራችን የዘመናዊ ትምህርት መጀመር ኢትዮጵያ ከሌላው አለም ጋር እንድትተዋወቅ ብሎም ከተኛችበት ጥልቅ እንቅልፍ ነቃ ብላ ሌላው አለም የደረሰበትን እንድትረዳ ትልቁን በር ከፍቷል። ዛሬም ቢሆን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ከተተበተብንበት የኋላቀርነት ውስብስብ ቋጠሮ ሊያወጣን የሚችለው አማራጭ መንገድ ትምህርት ነው።

በአግባቡ ከተጠቀምንበት ለማለት ያስደፈረኝ በአገራችን ዛሬ እግር ከወርች አስሮ አላንቀሳቅስ ያለንንና በየቀኑ የሰቀቀን ዜናዎችን እንድንሰማ ያደረገን ችግር ምንጮቹ ምሁራን የሚባሉት /ስለ አገር ብዙ ተስፋ የተጣለባቸው/የአገር ልጆች በራስ ፈቃድም ሆነ የሌሎችን አላማ ለማሳካት እየሄዱበት ያለው ጠማማ መንገድ በመሆኑ ነው።

ኢትዮጵያ ዘመናትን የተሻገረ ስልጣኔ፤ የራሷ አስተምህሮና የትምህርት ስርአት ያላት አገር ናት። አሁን ያለውን የስልጣኔ በጥራዝ ነጠቅነት እንድትቀላቀል ያስቻላት ከአውሮፓ የመጣው ዘመናዊ ትምህርት ነው። የአውሮፓው አስተምህሮ ደግሞ ወደአገራችን የገባው እዛው ሄደው በተማሩ የኛው ልጆችና በግብዣና በፈቃዳቸው ወደ አገራችን በገቡ የአውሮፓ ዜጎች ነው።

በተለይ ከ1960ዎቹ በኋላ የመጡ ምሁራን ከየተላኩበት አለም የቃረሙትን ርዕዮተ አለም አቅሟ በተዳከመው አገራችን ላይ ነባራዊውን ሁኔታ ከግምት ሳያስገቡ ሊተገብሩ ሲጣጣሩ አገራችንን መሽቶ በነጋ በቁልቁለት መንገድ ሲያምዘገዝጓት ቆይተዋል። እነዚህ የተለያዩ የአውሮፓ አገራትን ረግጠው የመጡ "ምሁራን" እንደ ሰለጠነ ሰው መደማመጥ ተስኗቸው፤ ብእራቸውን ወርውረው ነፍጥ በማንገባቸው የተነሳ የሀሳባቸውን መነሻም መድረሻም ያልተረዳ በርካታ የደሃ አርሶ አደር ልጅ ጭዳ ሆኖ ቀርቷል።

የእነሱ በሃሳብ መከፋፈል ሳያንስ በስራ፣ በማህበራዊ ህይወትና በተለይ በመምህርነት በአገር ውስጥ ሲያገለግሉ ይህንኑ አሻፈረኝ ባይነት በአገሪቱ እንዲስፋፋ አድርገውታል። ይህ «እኔ ብቻ አውቃለሁ» «እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን» እሳቤ ዛሬም ከስልሳ አመት በኋላ የአገር ውስጥ ዩኒቨርሲቲዎች ቁጥር ከአርባ በላይ በደረሰበት ወቅትም በኢትዮጵያ የተማረ ሰው መለያ ሆኖ ቀርቷል።

እያንዳንዱ "ምሁር" አንድ ቃል በተናገረ አልያም አንድ ቃል በጻፈ ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ የአብሮነት ገመድ እየላላ መምጣት ጀመረ ብል ማጋነን አይሆንም። ይኸው እኔ ብቻ አሸናፊ ልሁን ትንቅንቅን ስር እየሰደደ መጥቶ ዛሬ ዛሬ በበርካታ ወጣት አእምሮ ውስጥ እየተሰነቀረ እየረበሸን ይገኛል። እንዲህ አይነት የተጣመሙ እሳቤዎችን የነ አገር ተረካቢ በሆኑ በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም መመልከት አዲስ አይደለም።

አገር ወዳድ ትውልድ በመፍጠሩ ሂደት ምሁራንና ንቁ የምንላቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የችግር መነሻ ከመሆናቸው ባሻገር ለሚያምኑት ህዝብ ጀባ የሚሉትም የመፍትሄ ሀሳብ አዳማጭ ስለጠፋ ብቻ ሳይሆን ብዙ ግዜ ከውጪው አለም የተኮረጀ በመሆኑ ውሃ የሚቋጥር መፍትሄ ሲያስገኝልን አልታየም። በመሰረቱ የትምህርት አላማ ነገሮችን ሁሉ የሰው ልጅ ለራሱና ለወገኑ ወደ በጎ ነገር መለወጥ ማስቻል እንጂ ከሰውነት ተራ አውርዶ ባለ ቋንቋ እንስሳ ማድረግ አይደለም።

እውነት ለመናገር ዛሬ ዛሬ ትምህርት ቤቶች በተለይ ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን በስነ ምግባር አርቆ የማውጣቱ ጉዳይ የተሳካላቸው አይመስልም። ለነገሩ በየትምህርት መስኩ ተመርቀው የሚወጡ ልጆች ስለተማሩበትም ዘርፍ ምን ያህል መሰረታዊ እውቀት ይዘው እንደሚወጡ የሚያውቀው ፈጣሪ ብቻ ነው። ስለዚህ ትምህርት ተቋማት ይህንን የአገርን ህልውና ለማቆም የሚያስችል ኃላፊነትን ለመወጣት በቂ አቅም አላቸው ብዬ ለመናገር አልደፍርም። ነገር ግን አሁንም ቢሆን እያንዳንዱ ወጣት ለቤተሰቡ፤ ለአካባቢው ማህበረሰብና ለየሀይማኖት አባቶች የሚሰጠው ክብር የተሸረሸረ አይመስለኝም።

በመሆኑም ቤተሰብ ልጆቹን በመምከርና በመገሰጽ ለማረም ተመራጩ ወቅት አብረውት ብዙ ግዜ የሚያሳልፉበት ይሄ ክረምት ነው የሚል ትልቅ እምነት አለኝ። ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ማህበረሰቡም በተለይ የአገር ሽማግሌዎችና የኃይማኖት አባቶች ክረምትን ቤታቸው የሚያሳልፉ ተማሪዎችን የሚያርቁበት የሚቀርጹበት ሊሆን እንደሚገባም ይሰማኛል። በነገራችን ላይ ብዙዎቹ አገራዊ የሰላም እጦት ችግሮች መነሻቸው በትምህርትና በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ ያሉ ግለሰቦች ናቸው ብዬ ስለማምን እንጂ ተግባሪዎቹ በየመንደሩ ስራ ፈትተው የሚውሉ «የራስ ሀሳብ አልባ» ወጣቶች መሆናቸውን አልዘነጋሁትም።

በነገራችን ላይ ኢትዮጵያ ከምታስተናግዳቸው ብዝሃነቶች መካከል እንደ ምግብ እንደ አለባበስ በየአካባቢው ያሉ የግጭት አፈታት ስርአቶቻችንም ተጠቃሾች ናቸው። በኢትዮጵያ በቋንቋ ከተመዘገቡት ብሄረሰቦች ቁጥር በላይ የግጭት አፈታት ስርአቶች እንዳሉን ይታወቃል። እነዚህ የግጭት አፈታት መንገዶች የየራሳቸው የአከዋወን ስርአት ያላቸው ቢሆኑም ሁሉንም ከመነሻ አላማቸውና ከሚሰጡት ማህበረሰባዊ ፋይዳ አንጻር እንደሚከተለው ልናስቀምጣቸው እንችላለን።

በኃይማኖት ረገድም ልጆችን ልናርቅበት የሚያስችለን በቂ አስተምህሮዎች እንዳሉን ይታወቃል። ለዚህም የኃይማኖት አባቶችም ከእርስ በእርስ ፉክክር ወጥተው የነፍስ ልጆቻቸው ሰውን በሰውነቱ እንዲቀበሉ ፍቅርንና አብሮነትን እንዲያስቀድሙ ማስተማሪያው ግዜ አሁን ነው ብዬ አምናለሁ። በክረምቱ በየእምነት ተቋማቱ የኃይማኖት ትምህርት ለመስጠት የሚወጡት ማስታወቂያዎች ከላይ የጠቀስኩትንም ቢያካትቱ የተሻለ ነው።

ማህበራዊ ችግሮቻችንን ለመቅረፍ ማህበራዊ ተቋማቶቻችን መጠቀማችን ዘርፈ ብዙ ፋይዳ አለው። እነዚህ ባህላዊና ኃይማኖታዊ ስርአቶቻችን በአንደኛ ደረጃ ከማህበረሰቡ የፈለቁ በመሆናቸው ማህበረሰቡ በፈቃደኝነት አምኖ የሚተገብራቸውና የሚገዛላቸው መሆናቸው ሲሆን፤ በሁለተኛ ደግሞ በተለይ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርአቶች እንደ ፍርድ ቤት ለግጭቱ አካላት ለሆኑት ግለሰቦችም ይሁን ቡድኖች ጥፋተኛውን በመለየት ተገቢውን ቅጣት በመስጠት ለተበዳይ ፍትህ ከመስጠት ባሻገር የበዳይና የተበዳይ ቀጣይ ግንኙነት በቂምና በቁርሾ የታጀበ እንዳይሆን ግጭቶችን ከስር መሰረታቸው የመቅረፍ አቅም ያላቸው ናቸው።

በአንጻሩ በዘመናዊ መንግድ በህግ አግባብ ችግሮቻችን እንቅረፍ ብንል ከተደራሽነትና ከተነሳችሽነት ጀምሮ ያለንን አቅም ባለፉት ጥቂት ወራት በአገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የተከሰቱት ግጭቶች ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩን ይመስለኛል። ለነገሩ የህግ አስከባሪ አካላት ያላቸውን አቅም አሟጠው ይጠቀሙ እንኳን ብንል ከአገራችን የቆዳ ስፋት፤ ከህዝብ ብዛት፤ ከአሰፋፈር ሁኔታችንና ካላቸው የቁሳቁስ ግብአት አቅም አንጻር የትም መድረስ አይቻልም።

እናም ወላጆች የኃይማኖት አባቶችና በመንግስት መዋቅር ስር የሚገኙ የወጣት ማእከላትና የተለየዩ አደረጃጀቶች ሰው ሰው የሚሸቱ፤ ሰውን በሰውነቱ ብቻ የሚቀበሉና በምክንያት የሚኖሩ ልጆችን በመስከረም ወደትምህርት ገበታ እንዲልኩላት ኢትዮጵያ አበክራ ትጠይቃለች። ስለዚህ ሁላችንም በያለንበት የፍቅር፣ የመተሳሰብና የአንድነት ስንቅ አስይዘን ልጆቻችንን፤ ወንድምና እህቶቻችንን አሰንቀን አዲሱን አመት ለማስጀመር ዛሬ እንነሳ እልሀለሁ። ቸር እንሰንብት።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የኑሮ ውድነት ከንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ዐፄ ምኒሊክ እስከ ዘመነ ብልጽግና

**ክፍል ሁለት**

በክፍል አንድ ጽሁፌ የኑሮ ውድነት ከዳግማዊ ዐፄ ሚኒሊክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ እስከ ዘመነ ኢህአዴግ የነበረውን ለማየት ሞክሬያለሁ ። በዚሕ ጽሁፍ በዘመነ ብልጽግና ያለውን የኑሮ ውድነትና በመፍትሄው ዙሪያ አንድ ነገር ለማለት ሞክሪያለሁ ።

**የኑሮ ውድነት በዘመነ ብልጽግና**

የኢፌዲሪ ጠ/ሚ ክቡር ዶ/ር ዐብይ አሕመድ ስለኢትዮጵያ ከተናገሩት ጥቂቶቹ ላይ የሐሳብ ስንዘራ ኢትዮጵያ የሁላችን አገር፤ የሁላችን ቤት ናት። ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የአገሩን ጸጋና በረከት መጠቀም አለበት። ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ እንሆናለን። ኢትዮጵያዊ ሆኖ ለመኖር በሕይወት መቆየት ያስፈልጋል። ነፍስ ያለስጋ አትቆምምና።

የኢትዮጵያ ማኅፀን ለምለም ናት። እንኳን ዘር ተዘርቶ አይደለም ከወፍ አፍ የወደቀ ጥሬ በሚጸድቅበት አገር ላይ አርሶ መብላት ተስኖን በኑሮ ውድነት መሰቃየት የለብንም።

ፍትሕ ለንጹሃን ተገቢ እንደሆነ እናምናለን። ለአንድ አገር ብልጽግና አይነተኛ መሳሪያው ፍትሕ ነው። ፍትሕ ማጣት ፍቅርን ያነጥባል። ሰላምን ያደፈርሳል። መተባበርን ይፈታል። መደመርን አስትቶ ያነጣጥላል። እኛ ሳይሆን እኔ ያስብላል። ብዙዎች ለፍትሕ የተጋደሉት እኛነትን አስበው ነው። ዛሬ ለአገራችን የሚያስፈልገው እውነተኛ ፍትሕ ብቻ ነው።

የኑሮ ጣጣውም የነቃው ከፍትሕ መዛባት እንጂ በሌላ ተጽሕኖ ብቻ አይደለም። የሕዝብ መቸገር የዳንኪራ ያህል የሚያስፈነጥዛቸው፣ የሕብረተሰቡ አለመረጋጋት እንደአእዋፍ ጥዑም ዜማ የሚመስጣቸው ፍትሕን ገልብጠው በሚመሩ ንጹሕ ባልሆኑ የመንግሥት አካላትና ንጹሕ ባልሆኑ ባለሀብቶች ጥምረት ነው።

አንድ መንግስት ሥራ የሚሰራው ከሕዝብ ጋር በማበር ለራሱ ለሕዝቡ ቢሆንም፣ ሕዝብ የመሪውን ሕልም እንዲጋራና ታምኖ እንዲከተል በኑሮ ውድነት የተሳከረውን መንፈሱን ማብረድ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል። አንድ ሕዝብ እንጀራና ወጥን በሙሉ ኃይሉ ለፍቶ ማግኘት ከተሳነው የልማት መስመሩ ተንሸዋሯል ማለት ነው።

ትልልቅ አገራዊ የልማት ስራ የብልጽግና አጀንዳ ሰንቆ ከመንቀሳቀስ ጎን ለጎን ለኑሮ የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ነገሮችን በተጓዳኝ ማሟላት ተገቢ ነው። ዜጋው ኑሮ ቀንበር ሳይቀነስለት አንጀቱ በርሃብ እየተብላላ ልማት ብሎ ኒውኩለር ማብላያን ዐይነት ማሰብ የተሳካና ዘላቂ ውጤት አያመጣም። የኑሮ አለመቅለል ዜጋን ያሰድዳል። ተሰዳጅ ዜጋም ሲበዛ የሰው ሀብት ይናጠባል።

ለአንድ አገር የሰው ልጅን የመሰለ ቀዳሚ የተፈጥሮ ሀብት እንደሌለ የታመነ ነው። ዜጎች ዳቦ ተርበው ውሃ ተጠምተው ታርዘውና መጠለያ እርቆአቸው አገር ማልማት፣ ለአገር አርቆ ማሰብ፣ ባለዕራይ መሆን፣ ተምሮ የላቀ ውጤት ማምጣት፣ በጉልበት አገርን ማገልገል፣ በአገሪቷ ላይ ለነገ ሕይወት ዛሬን በተስፋ መኖር የማይቻል ነገር ነው የሚሆነው።

በኑሮ ውድነት ሕዝብ ተስፋ እየቆረጠ ልማትና ብልጽግናን፣ የአገር ፍቅርና ሰላምን ማምጣት ያስቸግራል። ዛሬም የአገራችን የንግድ ሥርዓት እንደከፉ ሱስ እየጨመረ ሄዷል እንጂ እራሱን አርቆና አስተካክሎ አልታየም። በአገር ውስጥ ተመርተው የሚቀርቡ ነገሮች እንኳን የዋጋቸው ማሻቀብ ለአመክንዮ የማይመች ነው።

ምርትም ኖሮ ምርትም ሳይኖር ሁሌም ኑሮና የኑሮ ጉዳዮች የነፍስ ያህል ውድ ይሆናሉ። ለምሳሌ ስኳር ጠፍቶ ዋጋ የጨመረ ሻይ ስኳር ሲገኝ እንኳን ከውድነት ክብሩ አይወርድም። በዚህ ስልት የተለያዩ ቁሶች፣ እህሉ፣ የቤት ኪራዩና ግዢው፣ የመኪና ሽያጭና የትራንስፖርት ዋጋው፣ አልባሳቱ፣ የትምህርት ቤት ክፍያው፣ የሕክምና ክፍያው፣ የሆቴልና የካፌ ዋጋ..... ሁሉም በዚህ አገር ላይ ለራሳቸው ክብር ፈጥረዋል።

በኑሮ ውድነት ጉዳይ ላይ የተነሱት ሐሳቦች በጊዜ እልባት ሊያገኙ ይገባል። በተለይ ስር ሰዶ ደሃው ሕዝብ ሊቆጣጠረውና ሊገበያየው ያልቻለው ከዕለት ፍጆታ እስከወር ቀለብ፣ ከተራ ቁስ እስከዐመት ልብስ .... በተመጣጣኝ ዋጋ ባለመሸመቱ ኑሮው የከፋ አድርጎታል። ሕዝቡ ተረጋግቶ በመኖር ምርትና ልማትን አፋጥኖ፣ ለነገው አትርፎ የሚኖርበት፣ ሥራ አጥ የሚቀነስበት፣ የጎዳናው ተዳዳሪ የሚጠፋበት፣ ለልመና የተሰማሩ ሕጻናት፣ ወጣቶችና አረጋውያን ወደ ኑሮ ሥርዐት የሚገቡበት .... እንዲሆን የሕዝቡ ኑሮ ይሻሻል ዘንድ ግድ ይላል። መንግሥትም የብዙኀኑ ሕዝብ ተግዳሮት የሆነው በሕይወት የመኖር የሕልውናን ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትልቁን ቁጥር የሚይዘው አርሶ አደር ሕዝብ ለዘመናት ከችግር አለመላቀቁ ጉዳይ እንደ አንድ ዐብይ ምስክር አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ምክንያቱም ገበሬው 80 ከመቶው የአገሪቷ ሕዝብ ሆኖ ሳለ አርሶ የሚያገኘው ምርት የዕለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን የማይሸፍን ከሆነ በወል አገራችን ችግር ውስጥ ናት ማለት ይችላል። ዛሬ ገበሬውና የገበሬው ልጅ ከማጀቱ ወጥቶ በየከተሞቹ በቤት ውስጥ አገልግሎት፣ በጉልበት ስራና ከዚያም ሲያልፍ በልመና ተሰማርቶ የሚገኘው የገጠር ኑሮው ተግዳሮት ቢሆንበት ነው። ለዚህ ችግር መፍትሔ የሚሆነው የግብርና ሥርዓታችን ለማጠናከርና ፍትሕን በማስፈን ነው።

**ጥቂት ስለመሬት ሀብታችን**

መንግሥት በድሃ ሆድ ውስጥ ለማደር የእርሻውንና የመሬት ሥርዐቱን በአጽንኦት ማየት አለበት። የኢትዮጵያ ቆዳ ስፋት ከአፍሪካ ከትልልቆቹ አንዷና ከዓለም ወደ 20ኛ አካባቢ ትሆናለች። በምሁራኑ የቁጥር ስሌት ደረጃ የአገሪቷ የመሬት ስፋት 111 ሚሊዮን ካሬ ያላት ሲሆን ከዚህ ውስጥ መታረስ የሚችለው ደግሞ 84 ሚሊዮን ካሬ ነው። ከግማሽ ክ/ዘ በፊት የታረሰው 13 ሚሊዮን ካሬ ነው። በዛ ዘመን የሕዝቡ ብዛት 30 ሚሊዮን ነበር።

ዛሬ ላይ ደግሞ እየታረሰ ያለው 16 ሚሊዮን ካሬ ሲሆን ልዩነቱ 3 ሚሊዮን ካሬ ነው። በዚሁ የእርሻ ውጤት ደግሞ በልቶ ለማደር የተፈጠረው የሕዝብ ብዛት ከ115 ሚሊዮን በላይ ነው። ለዛውም ለውጭ ገበያ ተልኮ የተረፈውን ነው ሕዝቡ የሚጠቀመው። ለእርሻ የተካለለው የመሬት ስፋት በ50 ዓመታት ውስጥ ያለለውጥ የተቀመጠ ነው። ዛሬ ላይ ያለው ሕዝብ እንጀራና ዳቦ በልቶ ለማደር መታረስ የነበረበት እስከ 50 ሚሊዮን ሔክታር የእርሻ መሬት ይመስለኛል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በገበሬው የኑሮ ዘይቤ ውስጥ የሚስተዋለው የመሬት ሥርዓት ደግሞ ወላጆች ልጆቻቸው ለጋብቻ ሲደርሱ ከማይጨመር የመሬት ሀብት ላይ ከጥማድ በሬ ጋር ለልጆቹ እየሸነሸነ ይሰጣል። ይህ አካኼድ ሁሌም የሚቀጥል አልሆነም። ለምሳሌ ዛሬ ላይ አርሶ መብላት፣ ጎጆ ቀልሶ መኖር የሚችለው የገበሬው የልጅ ልጅ ቁጥር መጠን ከአገሪቷ ሕዝብ ከግማሽ በላይ ሆኖ ሳለ ከወላጆቹ የመሬት ውርስ በማጣቱና ከመንግሥት የመሬት ምሪት ካለማግኘት የተነሳ በተለያዩ የክልል ከተሞችና በአገሪቱ መዲና ተሰዳጅ ሆኖ ሕይወቱን ይገፋል። ይባስ ብሎም በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የተለያዩ የውስጥ የርስበርስ ጦርነቶችና የጎረቤት አገሮች ትንኮሳና ጣልቃ ገብ ግጭትና ጦርነቶች ተዳምረው ውጤቱን የጓሮ አድርገውታል።

የዛሬ ወገብ የሚያጎብጥ የኑሮ ውድነት ለነገ መልስ የሌለው የሚበስል ጥያቄ ይዘን እንድንኖር የሚያደርገን የእርሻው የመሬት አስተዳደርና የግብርና መር የምጣኔ ሀብት ሥርዓታችን መዛባት ይመስላል። አገራችን ባላት የተለያዩ የአየር ንብረት አካባቢዎች መሬቶቹ የየራሳቸውን ዘር መስጠት የሚችሉ ናቸው። በዚህም ከ80 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መታረስ የሚችል መሬት ይዘን መሬቱንም ሕዝቡንም ጦም እያሳደርን ከድሃ ልክ ወርደን የድሃ ድሃ የኑሮ ደረጃ ሕዝብ አፈራን። የአገራችን የመሬት ሀብት ሌላውን አገራት መመገብ የሚያስችል ሆኖ ሳለ ቀድሞ ከነበሩ የንጉሣዊ ሥርዓት ጨምሮ የመሬት ሀብት የሕዝብ ሳይሆን የመሪዎች የሀብት ምንጭ የመደረጉ ውጤት በምግብ ራሳችንን እንዳንችል አድርጎናል።

መሬት በፊውዳል ሥርዓቶች ውስጥ የገበሬው ሳይሆን የነገሥታቱና የርዝራዥቻቸው ነበር ማለት ይቻላል። በዚህም ገበሬው ጭሰኛ ነበር። ወታደራዊ መንግሥትም መሬት ላራሹ ቢያሳውጅም የከተማውና የገጠሩ የመሬት ድርሻ ለስራና ለኑሮ እምብዛም ምቹ አልነበሩም ማለት ይቻላል፤ ምክንያቱም በመንግስት ቁጥጥሩ ስር ነበሩና። የኢሕአዴግ ዘመነ መንግሥትም የመሬት ፖሊሲው የበለጠ ወደራሱ በማድረግ የገጠሩም ሆነ የከተማው የመሬት ሀብት ትልቁ የመንግሥት ካዝና መሙያ ምንጭ አደረገው።

በዘመኑም ከአውሮፓ አገራት በላይ የመሬት ዋጋ በኢትዮጵያ ውድ ሆነ ተብሎ እስኪተች አደረሰው። በዘመነ ብልጽግናም የመሬት ፖሊሲ ላይ የተሻለ ብርሃን አልታየም። ይባስ ብሎም ገበሬው ከመቼውም በላይ ብዙ ነገሮች ተዳምረው የማዳበሪያ ዋጋ መቋቋም አቅቶት ባለችው ውስን መሬት እንኳን አርሶ መብላት ተግዳሮት ሆነው። ከተማውም በጥቂት የናጠጡ ሀብታሞች ቤተ መንግሥት ያህል መኖሪያ እየገነቡ ሲኖሩ ብዙኀኑ ድሃው ጎኑና ቁመቱ ፤ ዐይነትና ደረጃው በማይሻሻል የቀበሌ ቤት ጥገና ሆኖ ይኖራል።

ቢያንስ አያትና ቅድማያቶቹ የኖሩበት ቤት ውስጥ የሚኖር የከተማው ነዋሪ የራሱ ቤት አድርጎ ግብር ከፍሎ እንዲኖር አልተደረገም። ነዋሪው ቀበሌ ቤትን የራሱ ሆኖለት በጥሩ መልኩ አሻሽሎ መኖር ቢፈቀድለት በራሱ መንግሥትን በሰፊ ያግዘው ነበር። ይህም የፍትሕ አንዱ ጥያቄ ነው።

ኢትዮጵያ ሰፊ አገር ናት። ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለሌላውም የምትበቃ አገር ናት። የቆዳ ስፋቷ በምጣኔ ሀብት ኃያላንና በኑሮ ምቹ ከሆኑ ሦስት የአውሮፓ አገሮች ማለትም እንግሊዝ፣ ጀርመንና ፈረንሳይ ተደምረው የማይተናነስ የቆዳ ስፋት ያላት አገር ሆና ሳለ ገበሬው የሚያርሰው ከተሜው የሚኖርበት መጠለያ ማጣት ተገቢ አይደለም። ለዚህም የአገሪቱ መሬት ፖሊሲ ሊታሰብበት ይገባል።

የዛሬው ዐይነት የኑሮ ውድነትም የመጣው ከብዙ ምክንያቶች በላይ በእርሻው ላይ አጠንክረን ባለመስራታችን ነው። ዛሬ ላለው ችግር ማለፊያ ተደርጎ የተወሰደው የጓሮ አትክልት ከድሃው ጎጆ እስከ ቤተ መንግሥት ጓሮ ድረስ የሚያስተክል ርብርብ የመጣው ሌላውን ዓለም መመገብ የሚችል የመሬት፣ የውሃ ሀብት፣ የተፈጥሮ ምቹ የአየር ንብረትና 80 ከመቶ ያላነሰ ትጉ ገበሬ ባለባት አገር ግብርናውን ዞር ብለን ልናየው ይገባል።

**የሕዝብን ኑሮ ለማሻሻል ከመንግስት ቀጥሎ ዋና ባለድርሻ አካላት**

የአንድ አገር የኑሮ ዘይቤ የተሳካ እንዲሆን የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው መንግስት ቢሆንም የሕዝቡና የባለሀብቱ ሚና ቀላል የሚባል አይደለም

**ባለሀብት**

ባለሀብቶች ችግርን ሁሉ በገንዘብ ይለፍልኝ ብላችሁ የምታስቡ መሆን የለባችሁም። እናንተ ተግዳሮቱን መቋቋም በመቻላችሁ በቀላሉ የምትተውት የተዛባ የገበያ ሥርዓት በአገሪቱ ድሃ ኅብረተሰብ ላይ አሉታዊ ተጽሕኖ ያሳድራል። ምንም እንኳን ገንዘባችሁ የችግር በሮችን የምትፈቱበት መሳሪያ ቢሆንም በገንዘባችሁ አገሪቷንና የድሃውን ማኅበረሰብ የግብይት ሥርዐት ማዛባት ግን ተገቢ አይደለም።

ገበያ ወይም ንግድ ሥርዓት ነው። ሥርዓት ላይ ደግሞ ያፈነገጠውን በመደገፍ የሚደረግ አስተዋጾ የብዙኀንን ኅብረተሰብ የኑሮ እሴት ያበላሻል። ሁሌም ቢሆን ነገሮች መታሰብ ያለበት በተጠራቀመው ጥሪት ልክ ሳይሆን ነገሩ በጊዜው በያዘው እውነታ መሆን አለበት - በዋጋው።

የተሻለ ዋጋ መክፈል ያለበት ለቀላሉና ለተራው ነገር ሳይሆን እሴት ለተጨመረበት ነገር ነው። ልዩነታችሁን ከድሃው ማኅበረሰብ ጋር ማነጻጸርም ሆነ ማወዳደር የለባችሁም። ጉዳዩ በያዘው ልክ እንጂ። መቻል ዋጋ አውጥቶ መግዛት ብቻ ሳይሆን ዋጋው ነው ወይ? ብሎ ለዜጋው አስቦ፣ ለትውልድ ተገቢ ሥርዓት ዘርግቶ መገበያየት መቻል ከአንድ ዜጋ የሚጠበቅ ነው።

**ብዙኀን ሕዝብ**

በአንድ አገር መንግስት አገርን በሥርዓት ለመምራት የሚያወጣው ሕግና ደንብ ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ በመንግስት የሚተዳደረው ሕዝብም ለመንግስት ሥርዓት፣ ሕግና ደንብም ተገዢ ሊሆን እንደሚገባ ይታመናል። አንዳንዴ ደግሞ መንግስት ፈር ማስያዝ የከበደውን ነገር ከምንም በላይ ሕዝብ ሥርዐት ሊያሲዘውም ይችላል።

ትናንት በተመጣጣኝ ዋጋ የገዛነውን ቁስና የዕለት ፍጆታ ያለምንም እሴት ጭማሪና በነገሮቹ ላይ ምንም ዓይነት ዋጋ የሚያስቀጥል ምክንያት ሳይኖርበት ንጹሕ ያልሆነው ነጋዴ ባቀረበለት ዋጋ የሚሸምት ከሆነ ከምንም በላይ ኑሮው እንዲወደድ ትልቁን ድርሻ እየተጫወተ ያለው ራሱ ተጎጂው ማኅበረሰብ ነው።

አንድ ዳቦ ላይ ከነበረው ግራምና እሴት ሳይጨምር፣ በአገሪቷ ላይም የስንዴ ዋጋ ባልጨመረበት ሁኔታ ላይም እንኳን ዳቦው ከቀደመው ግራም ቀንሶ፣ ዋጋ ጨምሮ ለገበያ ሲቀርብ መሸመት ተገቢ አይደለም። በቀን ልዩነት ያለምንም ምክንያት እንደዱብ ዕዳ ዋጋ ጨምሮ ሲያድር ለምን? የማይል ሕዝብ ሊኖር አይገባም።

የኑሮ ውድነት አቀጣጣይና ተዋንያን ሆነን ስንተውን አንዳንዴ ድህነትን የምንወድ፣ መከራን የምንወድ፣ ችግር ሲከበን የማንደነግጥ፣ በሰራነው ሥራ ለነገው ትውልድ ሊገጥመው የሚችለውን ተጽሕኖ ቆም ብለን የማናስብ ዓይነት እንመስላለን። ዛሬ ዛሬማ በውድ ተመን ለሽያጭ የቀረቡ ቁሶችን ሆይ ሆይታ እየፈጠሩ ሰልፍ እያስረዘሙ፣ ነጋሪት እያስጎሰሙ፣ መለከት እያስነፉ፣ አዋጅ እያሳወጁ መገበያየት ዓይነት የሕዝብ የዕለት ተዕለት የዝና ስራ አይደለም።

አንዳንዶቻችን ኑሮን አቅልሎ ከመኖር ይልቅ አማራጭ ያለውም የሌለውም አስቸጋሪ በሆነም ባልሆነም ጊዜ ሆቴልና ሬስቶራንት እንጀራ ካልቆረስን፣ በየካፌው ሻይ ቡና ካልጠጣን፣ የቡቲኩን ፋሽን ካልለበስን፣ በየማጌጫው ቤት ቁሶች ካልደመቅን፣ ውድ ስልኮችን ካልያዝን፣ በኮንትራት ታክሲ ካልሄድን... ሰው የሆንን አይመስለንም። ኑሮና ሕይወትን ንጹሕና ቀላል በሆነ መንገድ መኖር መቻል ከሰው በታች የሆንን ይመስለናል።

የምንጫማቸው ጫማና የምንለብሳቸው አልባሳት፣ የምንገለገልባቸውና የምናጌጥባቸው ቁሶችን የዋጋ ውድነት ብቻ መተረክ የሰብዕናችን መለኪያዎች አይሆኑንም። በዝቅተኛና በተመጣጣኝ ዋጋ መገበያየት የበታችነት መለኪያም አይደለም። የኑሮ ልከኝነት እንጂ። ቲማቲም በስጋ ዋጋ የዘንድሮ ቲማቲም ደም አለው ወይ? አለች አንዷ የስራ ባልደረባዬ፣ ሽንኩርት በዶሮ ዋጋ፣ ኪሎ ስጋ በበግ ዋጋ፣ ዳቦ በእንጀራ ዋጋ መሸመት ኑሮን ማሸነፍ አይደለም። በኑሮ መሸነፍ እንጂ።

በዕለት ተዕለት የግብይትና አገልግሎት አጠቃቀም ሥርዓታችንና በሌሎችም ተዛማጅ ነገሮች ላይ በሥርዐት ልንኖር ይገባል። ቢያንስ በታወቁ መንግስት በተመነላቸው ታሪፎች በመገበያየት የኑሮውን ውድነት ልንታገለው እንችላለን። እንዲህ አይነት የኑሮ ዘይቤ ሁሌም በመንግስት አዋጅ፣ በጋዜጣዊ መግለጫ፣ በምክር ቤት ውሳኔ የሚስተካከል አይደለም። ሥርዓትን በማክበር የሚመጣ ነው። ሁሌም ውድ ነገር የትልቅነት መለኪያም አይደለም። ተገቢውን የገበያ ሥርዐት ማሰብና መፍጠር አሪፍነትና ዘመናዊነት ነው።

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ- አዲስ የግብይት ስርዓት

**ዳግም ከበደ**

በኢትዮጵያ የአገልግሎት አሰጣጥ ዘርፉን ለማዘመን የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ግንባታዎች በመንግስትና በግል ተቋማት ጭምር የማካሄዱ ስራ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠጨመረ መጥቷል። እነዚህ አማራጮች አንድን ጉዳይ ለማስፈጸም ይወስድ የነበረውን ጊዜን በከፍተኛ ሁኔታ በማሳጠር፣ አላስፈላጊ የገንዘብ ወጪን በማስቀረት እንዲሁም ጉልበትን እየቀነሱ ተገልጋዩን ከእንግልት እየታደጉት ይገኛሉ። ከሁሉም በላይ በዲጂታል አማራጭ የሚሰጡ የመንግስት አገልግሎቶች ጥራትን እንዲሁም የቁጥጥር ስርዓቱን ማቀላጠፍ እየቻሉም ናቸው። ዜጎች ዘመናዊ ኑሮን ለመምራት የሚያስችል ንቃተ ህሊና እንዲኖራቸውና ወደ እዚህ ስርዓት መግባት እንዲችሉ መንገድ ጠራጊ እንደሆኑም ይታሰባል።

ለእዚህም በፋይናንስ ቴክኖሎጂው (ፋይንቴክ) ረገድ በባንኮች የተጀመሩ ዲጅታል የክፍያ አማራጮችን ጥሩ ማሳያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል። በሞባይል ባንኪንግ መተግበሪያ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ በግል ባንኮችና በኢትዮ ቴሌኮም አማካኝነት የሚቀርቡ የፋይናንስ መተግበሪያዎች ረጅም ሰልፎችን ከማስቀረታቸውም በላይ ጊዜንና ከዚያ ጋር ተያይዞ የሚደርስ ብክነትን እና እንግልትን ያስቀሩ እንደሆነ ይታመናል። የአገልግሎት ዘርፉን በቴክኖሎጂ የሚደግፉ ሌሎች ዲጂታል አማራጮችም እንዲሁ የዚሁ አካል ናቸው። ከሁሉም በላይ ግን ኢትዮጵያ እያደረገች ያለችውን ዲጂታል ሽግግር የሚደግፍ ቀዳሚ ዲጂታል መሰረተ ልማት ስለመሆናቸው የቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ይመሰክሩላቸዋል። የዝግጅት ክፍላችን በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዱ ላይም ከላይ ከጠቀስናቸው የዲጂታል ስርዓቶች ውስጥ የሚካተት አንድ መረጃ ይዞላችሁ ቀርቧል።

እንደሚታወቀው በገበያ ስርዓት ውስጥ "ደረሰኝ" የሽያጭ አማራጭ እንደሆነ ይታወቃል። መንግስትም ሆነ ዜጎች በዚህ ማስተማመኛ የገንዘብ ልውውጥ በማድረግ ህጋዊ አካሄድን የተከተለ ግብይት ይፈፅማሉ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የደረሰኝ ጥቅም "በማንዋል" አሊያም በወረቀት ሽያጭ የሚካሄድ ነው። ይህም ማለት በካሽ ሬጅስተር (በወረቀት ሽያጭ) አሊያም ደግሞ በእጅ የሚቆረጥ ደረሰኝን የሚያካትት ነው። ይህ አካሄድ ደግሞ ግብይት ለሚያደርገው ተጠቃሚ ምቹ አይደለም። ለመንግስትም ይህን ስርዓት ተከትሎ የሚፈለገውን ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል አጋጣሚን የሚፈጥር አይደለም። በዚህ ምክንያት ዲጂታል ደረሰኝ አሊያም ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝን የመጠቀም አማራጭ አሁን አሁን አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል።

ብሩክ ገብረየስ የተቀናጀ የደራሽ ፕላትፎርም ዲቪዥን ዳይሬክተር ነው። ከዚህ ቀደም "በደራሽ" ፕላትፎርም ላይ ማብራሪያ ሰጥተውናል፤ አሁን ደግሞ በኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ አስፈላጊነትና በኢትዮጵያ ውስጥ በምን መንገድ ተግባራዊ ለማድረግ በመሰራት ላይ እንዳለ ያጋሩንን ማብራሪያ ይዘን ቀርበናል።

እንደ አቶ ብሩክ ገለፃ፤ ግብይትን ህጋዊ ከሚያደርጉ ስርዓቶች መካከል ደረሰኝ ዋንኛው ነው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ጥቅም ላይ እየዋለ ያለበት መንገድ በማንዋል አሊያም የወረቀት ልውውጥን ተከትሎ የሚካሄድ በመሆኑ ለተጠቃሚውም ሆነ ለመንግስት ምቹ አይደለም። በተለይ በመንግስት በኩል አስፈላጊውን ግብር ለመሰብሰብ እንዳላስቻለ ይገለጻል። ይህም ህገወጥ ነጋዴዎች ግብርን እንዲሸሽጉና እንዲያጭበረብሩ ምቹ ሁኔታ እንዲኖር አድርጓል።

"በአገራችን ከፍተኛ የሆነ የግብር መሸሸግ ወይም ማጭበርበር ይካሄዳል" የሚሉት የዲቪዥኑ ዳይሬክተር፤ በብዙ ቢሊየን ብሮች ለግብር ስወራና ማጭበርበር ተጋላጭ መሆናቸውን ይናገራሉ። ይህም ህዝብንና መንግስትን በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂ እንዳደረገ ይገልፃሉ። በተለይ በወጪና ገቢ ንግዱ ላይ ከፍ ያለ ካፒታል በህገወጥ መንገድ ከአገር እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን መቻሉን ነው የሚያስረዱት፡፡ በተለይ በወጪና ገቢ ንግዱ ላይ ከፍ ያለ ካፒታል በህገወጥ መንገድ ከአገር እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን መቻሉንም ያስረዳሉ። በዚህ ምክንያት ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝን በመጠቀምና በግብይት ስርዓት ውስጥ በቴክኖሎጂ አማራጭ ተፈፃሚ እንዲሆን በማስቻል ችግሩን ለማቃለል መንግስት እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ።

"እስካሁን በተቀናጀ የደራሽ ፕላትፎርም ደረሰኝ በዲጅታል አማራጭ እየቀረበ ይገኛል" የሚሉት ዳይሬክተሩ፤ ይህንን እንደ አንድ የቴክኖሎጂ አቅምና ተሞክሮ በመጠቀም በዋናነት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን ግብይት የተሳለጠ ለማድረግ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ጥቅም ላይ ለማዋል እየተሰራ መሆኑን ያመለክታሉ። በዋናነትም የተለያዩ አገሮች ልምድን በመውሰድ በአገር ውስጥ የቴክኖሎጂ ፕላትፎርም አበልፃጊዎች በዋናነትም በኢንፎርሜሽን መረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር አማካኝነት መፍትሄ ለመስጠትና ኤሌክትሮኒክ ደረሰኝ ለማቅረብ እየተሰራ መሆኑን ያስረዳሉ።

"ልክ እንደ ደራሽ ፕላትፎርም ለዜጎች የሚደርሱ አገልግሎቶች ኢንሳ ያቀርባል ማለት አይደለም" የሚሉት የዲቪዥኑ ዳይሬክተር፣ ይሁን እንጂ ይህን የዲጂታል አማራጭ ለግል ዘርፉ በአገር ውስጥ አቅም ያለማንም አካልና የቴክኖሎጂ ጥገኝነት ለማቅረብ እየተሰራ መሆኑን ነው የጠቆሙት።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ከዚህ ቀደም በደራሽ ፕላትፎርም ተከታታይ ቁጥር ያላቸው የመንግስት አገልግሎት የሚሰጡ ደረሰኞችን የማቅረብ ስራ ለማከናወን ቴክኖሎጂውን በኢንሳ በኩል የማበልፀግ ስራ ተከናውኗል፤ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ይፋ በሚደረገው "ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ" ደግሞ ማንኛውንም ግብይት አሊያም ሽያጭና ግዥን የሚፈፅም አካልን የሚያገናኝ ዲጅታል አማራጭ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሰራ ነው። ከመጀመሪያው ፕላትፎርምም በተጠቃሚና በሚሰጠው ግልጋሎት ይለያል።

ቴክኖሎጂው ከማንዋል የደረሰኝ ስርዓት የሚለየው የወረቀት አሰራርን በማስቀረቱና ለቁጥጥር ምቹ አማራጭ በመፍጠሩ ነው የሚሉት አቶ ብሩክ፣ በዋናነት ግን ህጋዊ የደረሰኝ መዋቅርን የተከተለ መሆኑንም ይገልፃሉ። ከባንክ "የፋይን ቴክ" ወይም እንደ ቴሌ ብር ያሉ መተግበሪያዎች እነዚህን ደረሰኞች ተጠቅመው ክፍያ ለመፈፀም የሚያስችሉ ይሆናል ይላሉ።

"ክፍያን ያለ ደረሰኝ በማንኛውም አገልግሎት መስጫ ተቋም ማስተናገድ በህግ የተከለከለ ነው" የሚሉት አቶ ብሩክ፣ በቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚፈፀሙ ክፍያዎች ደረሰኝ ሲኖር ብቻ ህጋዊ እንደሚሆኑ ይናገራሉ። በዚህ ምክንያትም በዲጂታል አማራጭ በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ ዛሬ ተሞክሮ በማያውቅ መልኩ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ጥቅም ላይ እንዲውል የመሰረተ ልማት ግንባታና ሌሎች አስቻይ ሁኔታዎች እየተዘረጉ መሆናቸውን ያብራራሉ።

እንደ አቶ ብሩክ ገለፃ፤ የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ በግብይት ስርዓት ውስጥ በቀላል አማራጭና ለተጠቃሚ ምቹ በሆነ መልኩ ለማቅረብ በኢንሳ በኩል እየተሰራ ይገኛል። በዚህ ስርዓት ውስጥ ተጠቃሚ የሚሆኑት አካላት በርከት ያሉ እንደመሆናቸው መጠንም ሰፊ የሆነ የቴክኖሎጂ አቅም የሚፈልግና የሚፈጥር ይሆናል። ከዚህም ባለፈ እጅግ በርከት ያሉ የንግድ ተቋማትን ከማስተሳሰሩም በላይ መንግስት የግብይት ስርዓቱን በቴክኖሎጂ አማካኝነት በቀላሉ ለመቆጣጠር ይጠቅማል።

የመረጃ መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢንሳ) ከተለያዩ ባባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ የሚያደርገው ኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ የንግድ ድርጅቶችም ሆኖ ክፍያን የሚፈፅሙ ማናቸውም ተቋማት በስርዓቱ ግብይትና ህጋዊ ደረሰኝ ልውውጥ እንዲያደርጉ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። እየበለፀገ የሚገኘው ሲስተምም ዋስትናው በተጠበቀ መልኩ የደረሰኝ አቅርቦት እንዲኖር ያስችላል።

"ይህ የዲጂታል ደረሰኝ በገበያ ስርዓት ውስጥ እንዲያልፍ ሲደረግ የሚያጋጥሙ ችግሮች አሉ" የሚሉት ዳይሬክተሩ፣ በተለይ ሁሉም የንግድ ተቋማትም ሆኑ ዜጎች ሙሉ ለሙሉ ተጠቃሚ እስኪሆኑ ድረስ ብዙ ውጣ ውረዶች ሊያልፍ እንደሚችል ያስረዳሉ። ይሁን እንጂ በቴክኖሎጂ ዙሪያ የሚሰሩ እንዲሁም ዲጂታል ደረሰኝ የሚያስፈልጋቸው ግብይት የሚያካሂዱ ተቋማት ቀዳሚ ተጠቃሚ እንደሚሆኑና ቀስ በቀስ እንደሚለመድ ያስገነዝባሉ።

እንደ አቶ ብሩክ ገለፃ፤ በኦላይን አማራጭ የዲጂታል ደረሰኝን የመሰሉ ፕላትፎርሞች ሲቀርቡ ብዙ አይነት አደጋን ሊያስከትሉ የሚችሉ አካላት ያጋጥማሉ። ይህን መሰል አገልግሎት በበይነ መረብ እስካቀረብክ ድረስ ተጋላጭነትህም ሰፊ ይሆናል። በተለይ ከፋይናንስ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ከሆነ ለጥቃት የመዳረግ ሁኔታው ከፍተኛ ነው። ይህን መሰል ፕሮግራሞችን ለማጥቃት ፍላጎት ያላቸው አካላትም በስፋት በዓለማችን ላይ አሉ። ይህን ጥቃት ለመከላከል ፕላትፎርሙን ዲዛይን ከማድረግ ጀምሮ ሊሰነዘሩ የሚችሉ ጥቃቶች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ታስቦ ነው የሚሰራው። ስለዚህ ከስሪቱ ጀምሮ ይህን ታሳቢ በማድረግ ነው እየተሰራ ያለው።




### እንደ መውጫ

ጉዳይ ኖሮን ወደ አንድ የመንግስትም ሆነ የግል ተቋም ስንሄድ በቅድሚያ የሚያሳስበን ነገር አገልግሎት ለማግኘት ስንል የሚያጋጥመን "ወረፋ ጥበቃ" ነው። ባለን ውስን ሰዓት ከአንድ በላይ ጉዳይ መፈፀም ሲኖርብን ደግሞ ጊዜያችንን የሚያቃጥለውን ወረፋ ባይገጥመን እንመርጣለን። በተለይ በመንግስት አገልግሎት ሰጪዎችና የክፍያ ቦታዎች ይህን መሰል ችግር በስፋት ያጋጥማል።

በዓለማችን የጊዜና ገንዘብ ብክነትንና እንግልትን ለማስቀረት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችና የክፍያ ስርዓቶች በስፋት ይታወቃሉ። የአሰራር ስርዓት የሚፈጥረውን እንግልት የሚቀንሱ ፕላትፎርሞች፣ መተግበሪያዎችና ሲስተሞችም ተመራጭነታቸው የሰፋና ጥቅም ላይ እየዋሉ የሚገኙ የዘመኑ አማራጮች ናቸው። ይህን መሰል ዲጂታል አገልግሎት በአገራችን እምብዛም አይታወቅም። አሁን አሁን የተሻሉ ሙከራዎች ይኑሩ እንጂ ቴክኖሎጂውን ለማበልፀግ የሚሰሩ ተቋማት ማግኘትም ያስቸግራል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብዙ ገንዘብ መሰብሰቢያ ተቋማት አሁንም በእጅ አሠራር ላይ የተመሰረቱ ናቸው፤ ደንበኞቻቸውንም ሒሳብ ለመክፈል በአካል እንዲቀርቡ ይጠይቃሉ። ይህ በሁለቱም በኩል ብዙ ችግሮችን አስከትሏል። ምክንያቱም ሰዎች እስከ አገልግሎት ሰጪዎች ቢሮ ድረስ መሄድ አለባቸው። በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ለፍጆታ፣ ለግብር እና ለሌሎች አገልግሎቶች ሂሳባቸውን ለመክፈል ረጅም ወረፋ ይጠብቃሉ። አንዳንድ ጊዜ የኢንተርኔት ግንኙነት፣ የመብራት መቆራረጥ ወይም በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ባሉ ሌሎች ምክንያቶች አገልግሎቱን በብቃት ማግኘት አይችሉም።

ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ግን በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢንሳ) አማካኝነት የሚደረጉ ሙከራዎች አበረታች ውጤቶች እያሳዩ ነው። ከእነዚህ መካከል የክፍያ ደረሰኞችን ለባንኮች ተደራሽ የሚያደርግ መድረክ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ ደረሰኝ ተዘጋጅቶ አገልግሎት ላይ እንዲውል እየተሰራ መሆኑ እንደ ምሳሌ መውሰድ እንችላለን።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የዓለም አቀፍ የገንዘብ ድጋፍና ብድር ሚስጥሩ ሲፈተሽ

**ምሕረት ሞገስ**

የዓለም ባንክ በኢትዮጵያ በጦርነቱ የተጎዱ አካባቢዎችን ለመልሶ ማቋቋሚያ የሚሆን የ300 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ ስምምነቱን እንደገለፀ ግንቦት 8 ቀን 2014 ዓ.ም ተነግሯል። የድጋፍ ስምምነቱ በአማራ፣ አፋር፣ ትግራይ፣ ኦሮሚያና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች በግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች ለመልሶ ግንባታና መልሶ ማቋቋሚያ የሚውል መሆኑም ተጠቁሟል። ባንኩ ሰኔ 8 አካባቢም በኢትዮጵያ በግጭት ምክንያት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት ለተዘጋጀ ፕሮጀክት የሚውል የ300 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ድጋፍ አጽድቆ ነበር።

በድጋሚም ባንኩ ግንቦት 30 ቀን 2014 በኢትዮጵያ የኮቪድ-19 ክትባትን ለዜጎች ለማዳረስና የጤና ዘርፉን ለማገዝ የ195 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ማድረጉም ከገንዘብ ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ ያመለክታል። በያዝነው ወር በሐምሌ 12 ቀን 2014 ዓ.ም ደግሞ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ለሰብዓዊ እርዳታ የሚውል 60 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ በዓለም ምግብ ፕሮግራም በኩል ለኢትዮጵያ ማድረጉ ታውቋል።

እነዚህን የመሳሰሉ ድጋፎች ቀደም ሲል መቀዛቀዝ ከታየባቸው በኋላ አሁን ላይ ለኢትዮጵያ የተለያዩ ተቋማት ድጋፍ ለማድረግ መነሳሳት የጀመሩት ለምንድን ይሆን? በማለት ያነጋገርናቸው የፖለቲካ እና የዲፕሎማሲ ምሁሩ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እምቢአለ በየነ ናቸው። ምሁሩ እንደሚናገሩት፤ አሁን ላይ እርዳታ እና ብድር የተገኘበትን ተጨባጭ ምክንያት በዝርዝር ለማስረዳት አስቸጋሪ ቢሆንም ነገር ግን በዋናነት ምክንያቱ ከሁለት አያልፍም ብለዋል።

አንደኛው የጦርነቱን የጉዳት ደረጃ በመገንዘባቸው ሊሆን ይችላል። ምናልባት አስከፊ የሆነ ሰብአዊ ቀውስ ከመከሰቱ በፊት ለመድረስ አስበው እርዳታውን እየሰጡ ነው ለማለት እንችላለን። ሁለተኛው ግን ከመንግስት ጋር ባደረጉት ስምምነት እርዳታ እና ብድር እየሰጡ ሊሆን ይችላል። ‹‹ይህ ስምምነታቸው ምንድን ነው?›› ከተባለ አይታወቅም። ለፖለቲካ ሲባል የማይገለፁ ስምምነቶች ሊሆኑ ይችላሉ። ይህም ቢሆን ግን እርዳታ እና ብድር የሚሰጡት ለውሃው ዘርፍ ልማት ለሕዳሴው ግድብ ሳይሆን ለሌሎች ወቅታዊ ጉዳዮች ለምሳሌ በጦርነት ለተጎዱት እና ለተፈናቀሉት ብለው እታች ድረስ ወርደው በሚከታተሉት አግባብ ሊደግፉ እንደሚችሉ መረሳት የለበትም ይላሉ።

በሌላ በኩል በአቶ እምቢአለ የተገለፀው፤ ዋነኛው ጉዳይ ሌሎች ግን የማናውቃቸው ነገሮች ሊኖሩ ቢችሉም ዓለም አቀፍ ተቋማት ከአባይ ተፋሰስ ጋር ተያይዞ እርዳታ እና ብድር የመስጠት ምንም አይነት ፍላጎት የሌላቸው መሆኑን ነው። በአባይ ተፋሰስ ላይ ለሚሠራ ማንኛውም ፕሮጀክት የዓለም የገንዘብ ድርጅት ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ልማት ባንክን ጨምሮ ማንም ቢሆን ድጋፍ ቀርቶ ምንም ዓይነት ብድር ለኢትዮጵያ አይሰጡም። ከውሃ ውጪ ባሉ ጉዳዮች ላይ ግን እርዳታ እና ብድር ይሰጣሉ። አሁን ግን አገር ውስጥ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ማለትም የሰሜን ጦርነትን ምክንያት አድርገው እርዳታ እና ብድር ለመከልከል ቢሞክሩም መነሻቸው የአባይ ጉዳይ መሆኑ መዘንጋት እንደሌለበት ያስገነዝባሉ።

‹‹ አጀንዳቸው የሕዳሴ ግድብ ነው። በዚህ ላይ በቀዳማይ ኃይለስላሴ ጊዜም ሆነ በደርግ ጊዜ እንዲሁም በኢህአዴግ ጊዜ የውሃውን ዘርፍ ደግፈው አያውቁም። ምክንያቱም እነዚህ የገንዘብ ተቋማት የአውሮፓ ሕብረት እና የእነ አሜሪካ ጉዳይ አስፈፃሚዎች በመሆናቸው የአገራቱን ሃሳብ መደገፍ፤ ማዕቀባቸውን የማስፈፀም ሥራን ይሠራሉ። በዚህ ሳቢያ የአውሮፓ አገራት ለኢትዮጵያ ብድር እና ዕርዳታ ሊሰጣቸው አይገባም ካሉ እነርሱም ምክንያት ፈልገው ሊከለክሉ ይችላሉ። ስለዚህ አሁን ዕርዳታ እና ብድር መስጠት የጀመሩበት ሌሎች የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ›› ብለዋል።

**ወደ ፊት የሚሆነውን የሚወስነው የኢትዮጵያ ሁኔታ ነው። ግድቡ አልቆ የፖለቲካ ሽኩቻው መላ ካገኘ እና ከተረጋጋ የሚፈለገውን አይነት እርዳታ እና ድጋፍ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በትብብር ለመስራትም ግብዣ የሚቀርብበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል**

እነ አሜሪካ ከመንግስት ጋር በአባይ ፖለቲካ ዙሪያ አስገዳጅ ውል ተፈራረሙ አትፈራረሙ ከሚለው ወጥተው፤ በሌላ በኩል አንዱ በሆነው ማስገደጃቸው ዶላራቸውን እየተጠቀሙ ነው የሚል ግምት እንዳላቸው አመልክተዋል። በሌላ በኩል ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ቀውሱን ተረድተው ችግሩ የበለጠ የከፋ ጉዳት ከማድረሱ በፊት ኃላፊነት እንዳለበት ተቋም ያንን ለማድረግ አስበው ሊሆን ይችላል የሚል ተስፋ እንዳላቸውም ገልፀዋል።

በተጨማሪነት አቶ እምቢአለ እንደሚሉት፤ ድጋፍም ሆነ እርዳታ ሰጪዎቹ ያስቀመጧቸው መስፈርቶች ይኖራሉ። ይህ ሲባል መንግስት ይህን ማድረግ አለበት ብለው ይወስናሉ። ያስቀመጡት ነገር ከአገር ውስጥ ሽብር ጋር ተያይዞ፣ ሕወሓትን በሚመለከት ወይም በህዳሴው ግድብ ዙሪያ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ከሕወሓት ጋር ስለመወያየት ሲነሳ በቅድሚያ አሸባሪ ተብሎ ስለተፈረጀ ሕወሓት ወደ ውይይት መግባት የለበትም የሚሉ ብዙ ሰዎች አሉ። ከሕወሓት ጋር ተያይዞ አንዳንድ ነገሮች መንግስት ይፋ ከማውጣቱ በፊት በሚስጥር ተይዘው ነበር። ያንን ያደረገው የሕዝቡን ምላሽ በመፍራት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ደግሞ የእርዳታ እና ብድር ሰጪዎቹን አቅጣጫ በመቀበል የተፈፀመ ሊሆን ይችላል የሚል ሃሳብ አላቸው።

መንግስት ከእነርሱ ጋር የተስማማባቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ ሲባል ከሕወሓት ጋር መደራደርን በሚመለከት ብቻ ሳይሆን ሌላም ነገር ሊኖር ይችላል ይላሉ። እና እጅ መንሻውን እያቀረቡ ይሆናል። የእነርሱን እጅ መንሻ ተከትሎ መንግስት ለሰላም ስንል ከማንም ጋር እንደራደራለን ብሎ ሊሆን ይችላል ሲሉ ግምታቸውን ያስቀምጣሉ።

‹‹አሜሪካንም ሆነች ሌሎች አገራት ሕወሓት ከአሸባሪነት መዝገብ መፋቅ አለባት የሚል እምነት አላቸው። በሌላ በኩል የይገባኛል ጥያቄ ያለባቸውን በሙሉ እንዲመለሱ የማድረግ ፍላጎት አላቸው። አንዳንዴ የትግራይ መንግስት እና የኢትዮጵያ መንግስት እስከማለት ይደርሳሉ። ይህንን የሚሉት ለመነጣጠል ነው። ከዛ አንፃር እነርሱ ፈፅሙ የሚሉት ነገር እስከዚህ ሊዘልቅ ይችላል።›› የሚል ሀሳባቸውን ያስቀምጣሉ።

ሌላው በጦርነቱ የደረሰውን ጉዳት ለመዘገብ የተለያዩ ጋዜጠኞች ከአውሮፓ መጥተዋል። አማራ ክልልም ሆነ አፋር ክልል ላይ የደረሰውን ጉዳት በአካል ሔደው አይተው ፅፈዋል። ባህርዳር ላይ መነሻ ፅሁፍ ሁሉ አቅርበዋል። ሚዲያው የተወሰነ ሽፋን ማድረግ ስለጀመረ ምናልባት ጉዳቱ ተሰምቷቸውም እርዳታ እየሰጡ ሊሆን ይችላል ይላሉ።

የሕዝብ ተወካዮች የ2014 ዓ.ም 6ተኛው ምክር ቤት የአንደኛ ዓመት የሥራ ዘመን 16ኛው መደበኛ ጉባኤ ከሕወሓት ጋር ስለሚኖረው የሠላም ድርድር ጥያቄ ቀርቦላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ፤ የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ሁልጊዜም ለሰላም ቅድሚያ ይሰጣል ማለታቸው ይታወሳል። “ ነገር ግን ለሰላምም ይሁን ለጦርነት የምንወስነው በብሔራዊ ጥቅማችን ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያን አንድነትና ጥቅሟን በሰላማዊ መንገድ ማስጠበቅ ካልተቻለ የህይወት ዋጋ ከፍለን በመስዋዕትነት ለማስጠበቅ ዝግጁ ነን። ነገር ግን በምንም መልኩ መንግስት በሰላማዊ አማራጭ ተወያይቶ መፍትሔ ለማምጣት ፈቃደኛ ከመሆን በተጨማሪ በዋናነት ለሰላም ቅድሚያ እንደሚሰጥ መዘንጋት የለበትም” ብለዋል።

እንደ አቶ እምቢአለ ገለፃ፤ ከእርዳታ እና ብድር ለመላቀቅ መፍትሔው ውስጣዊ ሁኔታ ማስተካከል ነው። ይሔ በሃይማኖት እና በብሔር ውስጥ ያለው ሽኩቻ ቀርቶ በአንድነት መቆም ከተቻለ የእነርሱን አቋም የሚወስነው የውስጥ ወቅታዊ ሁኔታ በመሆኑ የሚያሳስብ አይደለም። እነርሱ ጫና ለማሳደር የሚሞክሩት ውስጣዊ ሁኔታ እያዩ ነው።

‹‹የአባይም ሆነ ሌላው ፖለቲካ የሕዳሴውም ጭምር ለምን አሁን ተወሳሰበ ከተባለ እርስ በእርሳችን በመተረማመሳችን ነው። መንግስትም የተዳከመ ስለመሰላቸው ጉዳያችንን የምናስፈፅመው ዛሬ ነው። አጀንዳችንንም የምናስፈፅመው ዛሬ ነው። ብለው ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር አካባቢ የማራቅ የአባይን ውሃ እንዳትጠቀም የማድረግ ሥራን ይሰራሉ።›› ካሉ በኋላ፤ ኢትዮጵያ የፓን አፍሪካ ሞተር መሆኗን የሚጠሉም ብዙ አሜሪካንን ጨምሮ ምዕራባውያን በመኖራቸው የግብፅ እና ሱዳን አቋም እንዳለ ሆኖ የእነርሱም አቋም ከኢትዮጵያ እድገት ተፃራሪ መሆኑ ሁሉም ማወቅ አለበት ይላሉ።

ኢትዮጵያ ማደግ እንደሌለባት ብዙ ሰዎችም ፅፈዋል። ያንን በራሳቸው መፈፀም አይችሉም። ስለዚህ በኢትዮጵያ አስቻይ ሁኔታ ተፈጥሯል ብለው እየሰሩ እንደሚመስላቸው ተናግረው፤ ይህንን ተረድቶ ሁኔታዎችን መቀየረ ከተቻለ ወደ ፊት የሚስተካከል ይሆናል ብለዋል።

ነገር ግን የእጅ አዙር ጦርነት ከቀጠለ እርዳታም ቢሰጡ የሆነች የጎደለችውን ነገር ለማሟላት እንጂ በትክክል ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ስለማይሆን መፍትሔ ለማግኘት ኢትዮጵያ በራሷ መጣር እንዳለባት አስረድተዋል።

ዋነኛው መፍትሔ ‹‹ የሕዳሴ ግድቡን ጨርሰን፤ ግድቡ በሙሉ ሃይሉ ማመንጨት እና መጠቀም ከጀመርን ምናልባት አንድነታችን የሚጠናከርበት ሁኔታ ስለሚፈጠር እነ ግብፅም ሆኑ እነ አሜሪካ ይህንን አስገዳጅ ስምምነት ካልፈረመች እያሉ የሚጮሁትን በተወሰነ ደረጃ የሚያስታግስላቸው ይሆናል። ›› ያሉት አቶ እምቢአለ ከዛም በኋላ እርዳታ እና ብድር ማጣት ብዙ አሳሳቢ ላይሆን እንደሚችል ያመላክታሉ።

እንደ አቶ እምቢአለ፤ ወደ ፊት የሚሆነውን የሚወስነው የኢትዮጵያ ሁኔታ ነው። ግድቡ አልቆ የፖለቲካ ሽኩቻው መላ ካገኘ እና ከተረጋጋ የሚፈለገውን አይነት እርዳታ እና ድጋፍ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በትብብር ለመስራትም ግብዣ የሚቀርብበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።

የውስጥ ፖለቲካውን ለማረጋጋት የኑሮ ውድነት ችግርን መፍታት፣ መልካም አስተዳደርን እና ሙስናውን መቆጣጠር፤ መንግስት በትክክል የህዝብ አገልጋይ እንዲሆን በማድረግ ዘላቂ መፍትሔ ማበጀት ከተቻለ ኢትዮጵያን ከእርዳታ እና ብድር ማላቀቅ አዳጋች አይሆንም።

የህዳሴው ግድብ ሲያልቅ እነዚህ ካልፈረማችሁ እያሉ የሚጣደፉ አካላት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ጫና የሚያሳድሩ አካሎች ዜሮ ይሆናሉ። የህዳሴው ግድብም ኢትዮጵያን ከብዙ ብድር ከማዳን በተጨማሪ ኃይል በመሸጥም እንደተባለው እስከ አንድ ቢሊየን ዶላር በዓመት በማግኘት የሃብት ምንጭ ማድረግ ስለሚቻል የወደፊቱን ተስፋቸውን ያመላክታሉ።

በተቃራኒው የህዳሴው ግድብ ግንባታ በተራዘመ ቁጥር ወጪው ስለሚበዛ እና የውጪ ምንዛሬ ችግር ስለሚቀጥል በሌላ አገራት ብድር እና እርዳታ ላይ በመንጠላጠል የሌሎች ተፅዕኖ ተጋላጭ የመሆን ዕድል ሊያጋጥም እንደሚችል ያስረዳሉ።

ስለዚህ ትልቁ መፍትሔ የሕዳሴ ግድብን መጨረስ በኢኮኖሚ ላይ የሚፈጥረውን ጫና ቀንሶ ራሱ ገቢ የሚያስገኝ ይሆናል። የሥራ ዕድል እና ሌሎች የቱሪዝም መስኮች ተጨማሪ የገቢ ማግኛ ዕድሎችንም ያመጣል።

በተጨማሪ አሁን ላይ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ችግሮችን መቆጣጠር ከተቻለ በትክክልም ሉአላዊ አገር መሆን አያዳግትም። አሁን ግን በጀቱ ከሌላ ሆኖ ሉዑአላዊ አገር ነን ማለት እንደሚያዳግት በመጠቆም፤ እውነተኛ የሆነ ሉዑላዊ አገር ለመሆን የምግብ እና የኢነርጂ ዋስትናችንን ማረጋገጥ እና ለህዝብ የሚቆረቆር ስርዓትን መዘርጋት ዋነኛው መፍትሔ መሆኑን ይናገራሉ።

ከአቶ እምቢአለ በተጨማሪ ሌሎችም ምሁራን እንደሚገልጹት፤ አሁን ላይ እርዳታ እና ብድር መስጠት የተጀመረው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆኑም ምናልባትም መንግስት ለሰላም የሰጠውን ዋጋ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አላቸው። በዲፕሎማሲው ዘርፍ የተሰራው ስራና የተገኘው ውጤትም ሊሆን እንደሚችል ይገምታሉ።

ነገር ግን ከውጪ ምንም አይነት ብድርና እርዳታ ላለመፈለግ መፍትሄውና ቀዳሚው ስራ የአገር ውስጥ ገቢን ማሳደግ ነው። የመሠረተ ልማት እና የሰብዓዊ ልማት ፍላጎትን በዕርዳታ እና ብድር ላይ ከመመስረት ይልቅ በራሳችን ክፍያ መፈጸም እና የበጀት ጉድለታችንን ለማስተካከል የግብር ገቢን ማሳደግ ያስፈልጋል የሚል እምነት አላቸው ።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ኢትዮጵያ ለዓለም ገበያ የምታቀርበው ሸቀጥ ቀንሶ የምትሸምተው በመብዛቱ ምክንያት በ2017 ዓ.ም. የበጀት ጉድለቷ ጭማሪ አሳይቷል። በገቢ ማሽቆልቆል ሳቢያ ይኸው የበጀት ጉድለት እየሰፋ ቆይቷል። ይህም ኢትዮጵያ የገባችበትን ጦርነት ተከትሎ የተፈጠረባት የተወሳሰበ ችግር እንዲሁም ቀድሞም ቢሆን የተጠራቀመባት የዕዳ ጫና አሁንም ድረስ ላለችባት የበጀት ጉድለት መንስኤ ሆኖ የቀጠለ መሆኑን የሚናገሩት ምሁራኑ፤ የኢትዮጵያ ችግር ሌላኛው መፍትሔ የምጣኔ ሐብት ፖሊሲዋ ላይ የምትወስዳቸው እርምጃዎች ሊኖር እንደሚገባ ገልፀዋል። ኢኮኖሚዋ ከተሻሻለ የወደፊት እርዳታም ሆነ ብድር የማያሳስባት መሆኑንም ነው ምሁራኑ የሚስማሙት።

አዲስ ዘመን | ማክሰኞ ሐምሌ 19 ቀን 2014 ዓ.ም

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ጦርነት ያልበገረው የሴቶች የለውጥ ጉዞ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ጦርነት ሰዎችን ለከፍተኛ ሥነ ልቡናዊና አካላዊ ስቃይ የሚዳርግ መሆኑ ነጋሪ አያሻውም። በተለይም በሴቶች ላይ የሚያደርሰው ጉዳት ተዘርዝሮ የማያልቅ እንደሆነም እንዲሁ። ዘላለማዊ ጠባሳን የሚጥልና ቀና ብለው እንዳይሄዱ የሚያደርግም ነው። ለዚህ ደግሞ ጾታዊ ጥቃት ብቻ ማሳያ ነው። ዘርፈ ብዙ ጉዳቶችን ይዞ ይመጣባቸዋል። ጉዳዩን ለማንሳት ያስገደደን ደግሞ የዛሬ አመት ገደማ ከአሸባሪው ሕወሓት ጋር በተደረገ ጦርነት የተነሳ በተለያዩ አካባቢዎች በሴቶች ላይ የደረሰው ስቃይና መከራ ነው። በዚሁ ጦርነት ብዙ ጠባሳ ከጣለባቸው ከተሞች አንዷ ደሴ በመሆኗ በዚህች ከተማ ሴቶች ምን አይነት ፈተና እንዳሳለፉ አንድ ባለታሪክን መነሻ በማድረግ ልናወጋችሁ ስለፈለግን ነው።

አንድ ዓመት ከመንፈቅ ባስቆጠረው ጦርነት ብዙ ነገሮች እንደአገር ተከስተዋል። ብዙዎችን የሕይወት ምስቅልቅል ውስጥ ከቷቸዋል። ተረጋግተው እንዳይቀመጡም አድርጓቸዋል። ከዚያ የትም አንሄድም ብለው ለመቀመጥ የሞከሩት ደግሞ በረሃብ ተጠብሰዋል። ለልጆቻቸው የሚያቀምሱት አጥተዋል። ከእነዚህ መካከል ደግሞ ለዛሬ የሴቶች አምድ እንግዳ ያደረግናት ወይዘሮ ስመኝ በቀለ አንዷ ነች። ጦርነቱ ከሴቶች ጋር በተያያዘ ያስከተለውን ችግር ራሷን አብነት አድርጋ አጫውታናለች።

ስመኝ እንደምትለው፤ ጦርነት ወንድ ሴት ላይል ይችላል። ምክንያቱም ሁሉንም ያጠፋል፤ ያሰቃያል። ከአቅምና ከተፈጥሮ አንጻር ሲታይ ግን ሴቶች ላይ የበለጠ በትሩ ይጠነክራል። ከዚህ አንጻር ጦርነት በደሴ ከተማ ብቻ በሴቶች ላይ የፈጠረው ቁስል በቀላሉ የሚሽር አይደለም። ሴቶች የቤት ውስጥ ኃላፊ እንደመሆናቸው በጦርነት ወቅትም ቢሆን ቤተሰቦቻቸውን አብስሎ የማብላት ባህላዊ እዳ የተጣለው በእነርሱ ጫንቃ ላይ ነው። ብቻቸውን ሆነው ብዙ ተግባራትን ያከናውናሉ። የቤተሰቡ ቁጥር ሲሰፋ ደግሞ ድካማቸውም የዚያኑ ያህል ይከብዳል፤ ውሃ መቅዳት፣ እህል ማስፈጨት፣ ማገዶ መሰበር፣ ልብስ ማጠብ፣ የቤት ንጽህናን መጠበቅ፣ ልጅ ማሳደግ፣ በአመዛኙ በሴቶች ሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፤ በጦርነት ወቅት እነዚህን ተግባራት ማከናወን አንድ ፈተና ቢሆንም ጦርነቱ በርካታ ነገሮችን ማውደሙን ተከትሎ የሚፈጠረው የመሰረታዊ ፍላጎቶች እጥረት ሌላው ፈተና ነው።

በደሴና አካባቢዋ ጦርነት በነበረበት ወቅት ችግር ከነበሩት ጉዳዮች አንዱ የመብራት አለመኖር ነው። እህሉ እንደምንም ብሎ ቢገኝ እንኳን ማስፈጨት አይቻልም። ለማብሰል ደግሞ እንጨት መስበር ወይም መግዛት ግዴታ ነው። ይህንን ለማድረግም እድል አይኖርም። ስለዚህን ወቅት ታዲያ ቤት ያለው ሰው በሙሉ በረሃብ አለንጋ ይገረፋል፤ ስለዚህ ሴቶች በዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ሆነው ቤተሰቦቻቸውን ለማቅመስ መታተራቸው አይቀርም።

ሌላው ብርሃን የማግኘት ጉዳይ ሲሆን፤ ይህንን ለመሸፈንም ሻማ አለያም ክብሪት መግዛት ያስፈልጋል። በጦርነት ወቅት ሱቆች አገልግሎት ስለማይሰጡ አንድ ክብሪት በ20 ብር እስከመሸጥ ደርሶ ስለነበር ሕይወት በይበልጥም በሴቶች ላይ አስቸጋሪ ሆኖ እንደነበር ታስታውሳለች።

ደሴ ላይ ሌላው አስቸጋሪ የጦርነት ገጽታ የውሃ እጦት ሲሆን፤ ለመጠጥ የሚሆን ውሃ ለማግኘት እስከ 50 ብር ድረስ አውጥቶ መግዛትን ይጠይቅ ነበር፤ እሱም ከተገኘ። ይህ ደግሞ ለሴቶች ምን ያህል ከባድ እንደነበር መገመት አያዳግትም። ምክንያቱም ሴት ልጅ ንጽህናዋን ለመጠበቅ ከሌላው በበለጠ ውሃ ያስፈልጋታል። ግን በነበረው ሁኔታ ይህን ማድረግ አዳጋች ነበር። ከእርሷ በላይ ለሌሎች የምታስበው እናት የምትገዛውን ውሃና ምግብ ጭምር ለሌላው እየሰጠች ስትሰቃይ እንደነበርም የቅርብ ጊዜ ትዝታዋ መሆኑን ታነሳለች።

በጦርነቱ ሌላው ከባዱና ልትቋቋመው ያልቻለችው ነገር የጾታዊ ጥቃቱ ጉዳይ እንደነበር የምታነሳው ስመኝ፤ ስቃዩ ከባድ መሆኑን ታወሳለች። እርሷ በአካል ባታያቸውም ይህ ጉዳት የደረሰባቸው ሴቶች በአካላዊም በስነልቦናም መጎዳታቸውን ትገነዘባለች። ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች መጠቃታቸው ሳያንስ ማህበረሰቡ ስለሚጠቋቆምባቸው የልብ ስብራታቸውን በቀላሉ የሚጠግንላቸው አይሆንም። በዚህም ራሳቸውን



የሚያጠፉ እንደነበሩም ሰምታለች።

ሌላው ጦርነቱ ካበቃ በኋላ ያለው ሁኔታ ሲሆን፤ ኑሮን ለመግፋት ተንቀሳቅሶ መሥራት ግድ ቢሆንም ከደረሰባቸው ስቃይና ጉዳት አንጻር እንደልብ ለመውጣት ተቸግረው እንደነበር ትናገራለች። አሁን እያደር ነገሮች እየተረጋጉ ሲሄዱ ሁኔታዎች ቢቀየሩም ጦርነቱ እንዳበቃ አካባቢ ግን በፍራቻ ብቻ ለርሃብ የተጋለጡ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ታነሳለች። በዚያ ላይ ነጋዴው ጦርነት ተከሰተ በሚል ችግሮችን እየደረደረ በእቃዎች ላይ የማይገባ ዋጋን ይጨምራል። ሰላም ነው ቢባል እንኳን በአለማመን ውስጥ ያለንና ያልሰራን ሰው በዚህ መልኩ ማሰቃየት ደግሞ እጅጉን ያሳዝናል። እናም የሴቶች ፈተና በዚህ መልኩ ቀጥሏል ትላለች።

ጦርነቱ ያሳረፈው ጠባሳ ቢኖርም በዚያ ውስጥ የሚሯሯጡና ኑሮን ለማሸነፍ የጣሩ ሴቶችም ጥቂቶች አልነበሩም የምትለው ስመኝ፤ የጦርነቱ አለንጋ ሳይበግራቸው ደፋ ቀና እያሉ ቤታቸውን የሞሉ፤ ልጆቻቸውን ያበረቱና ጠላት እንዲመከት መከታ የሆኑም ሴቶች ነበሩ። ቁስላቸው ባይድንም ሕይወት ይቀጥላልና ከፍራቻ ይልቅ በአለው መረጋጋት ውስጥ መሥራትን የመረጡም ጠንካራ የወደፊት ተስፋ አብሳሪ ሴቶች እንደነበሩ በዚያ ጦርነት ውስጥ እንደታዩም ታወሳለች።

እርሷም ብትሆን ጦርነቱ አበቃ፤ አሸባሪው ሕወሓት ደሴን ለቀቀ ሲባል ጀምራ የእለት ጉርሷንና የቤተሰቧን ጉሮሮ ለመሙላት 11 ሰዓት ወጥታ ምሽቱ ድረስ መሥራትን እንደጀመረች ታነሳለች። ምክንያቱም በአለው ሰላም ውስጥ ሆኖ ራስን መለወጥ ካልተቻለ ጦርነት ኖረም አልኖረም ህይወት ፈተና መሆኑ አይቀሬ መሆኑን ስለምታምን ነው። ከጦርነት ስሜት ወጥቶ አለመስራት ሌላኛውን የድህነት ጦርነትን በራስ ላይ መክፈት እንደሆነም ስለምታውቅ ነው።

ወሎ አማራው ከኦሮሞው ጋር ክርስቲያኑ ከሙስሊሙ ጋር ተዋዶ እንጂ ተጣልቶ የማያውቅባት ምድር ናት። አሻግሮ የሚያሻግርም ሕዝብ ባለቤት ናት። እናም ዛሬ ይህ ቢገጥመንም ነገ የተሻለ ይኖራልና ከመቆዘም ይልቅ መሥራት ላይ ልዩ ትኩረታችንን ልናደርግ ይገባናል ትላለችም። ለዚህ ደግሞ ህመማቸውን እየቻሉ ቀደም ሲል የጀመሩትን ሥራቸውን አጠናክረው የቀጠሉትን ሴቶች አብነት እናድናደርጋቸው ስትልም ትናገራለች።

ከጦርነት በኋላ ወለዬዎች ምንም እንደማይበግራቸው ያየሁት ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ጭምር ከሕመማቸው በጥቂቱ እንዳገገሙ ወደ ሥራ መግባታቸው ነው። የቻሉትን ያህል እየተፍጨረጨሩ መሆናቸው ደግሞ ያስመሰግናቸዋልም ትላለች።

እርሷም ወደ አረብ አገር የሄደችው ያለ አባት ያሳደጓትን እናቷን ለማገዝ ነበር። በዚያ ግን ብዙ የሚያስተምሯትን ነገር አይታለች። አንዱ በችግር ውስጥ ሆኖ እንዴት መስራት እንደሚቻል ነው። ከጦርነት በኋላም ቀጥታ ወደ ሥራ ለመግባቷ መሰረት ሆኗታልና የሰው አገር ልምዷ እናቷ በአካባቢው ዘንድ የሚታወቀውና ደሴ የገባ ሰው ሳይሸምተው የማይወጣውን የወሎ ጭስ እየነገዱ ያሳዩዋትን ሥራ አጠናክራ እንድትቀጥልም ይህ ልምዷ አግዟታልና ታመሰግነዋለች።

ሥራው ዝቅተኛ ገቢ የሚያስገኝ ቢሆንም ማንም ተርቦበት ግን አያውቅም። ማንም ቢሆን አይታረዝበትም። ይልቁንም ለሌሎች ሰዎች ጭምር ተርፎ ሲደጎምበት ይታያል። ለዚህ ደግሞ ዋና መንስኤው በመረዳዳት ውስጥ አብሮ ከፍ ማለት እንዳለ ታውቆ መሰራቱ ነው። አሁንም ይህንን የመረዳዳት ባህል አንግበው ጦርነቱ የጣለውን ጠባሳ ማከም እንደሚገባ ትናገራለች።

እናቷን በሞት እንደተነጠቀች ስትሰማ ወደ አገሯ የተመለሰችው ስመኝ፤ ከአረብ አገር ስትመለስ ብዙም ገንዘብ አልነበራትም። የእርሷ ታናናሾችም አሉ። ስለዚህም እነርሱንም ሆነ ራሷን ለመደጎም መስራት እንዳለባት በማመን የእናቷን ሥራ አስቀጠለች። የእርሳቸውን መደብ በመረከብም ነው ጉልት ላይ ቁጭ ብላ የምትነግደው። በዚህ ሥራ የፈለገችው ግብ ላይ እንደምትደርስ እምነቱ አላት። ምክንያቱም ኢትዮጵያን፤ ወሎን የምታውቃት በመረዳዳትና አብሮ በመሻገር ነው። ስለሆነም ይህ ጊዜ ያልፋልና እርስ በእርስ መተካከሙ ላይ መበርታት እንደሚገባም ታስረዳለች።

ነጻነት ኖሮ በአገር ላይ ዝቅ ብሎ መስራት ከተቻለ መቼም ቢሆን ከፍ ማለት አይቀርም የምትለው ስመኝ፤ ጦርነቱ ያደቀቀውን ሀብታችንን ዳግም ለመመለስ ከሁሉም በላይ መሥራት ላይ ማተኮር ያስፈልጋል። መቆዘሙ መቼም ሊያነሳን አይችልም። የእኛን ማንነት የማይመጥኑ ብዙ ነገሮችን አይተን ይሆናል። ነገር ግን እነርሱንም መመለስ የምንችለው ሰርተን ብቻ ስንለወጥ ነውና ይህንን እልህ አስጨራሽ ፈተና በሥራ ማሸነፍ ይገባናልም ባይ ነች።

«አሁን በአገራችን ብዙ ነገሮች ተለውጠዋል። እንዳለፈው የመተባበርና የመተጋገዝ ባህሉ እየቀነሰ መጥቷል። ነጋዴው ትርፉን እንጂ ሰውን እያሰበ አይደለም። በብሔር መከፋፈሉና የእኔ ታላቅ ነው ባዩም በዝቷል። የተቸገሩትን ማየቱም እንብዛም ነው።» የምትለው ስመኝ፤ የራስ የተባሉት ሰዎች (ነጋዴዎች) ሕወሓትን አይዞህ የሚል ወኔን ሰጥተውታል። ዜጎች በኑሮ ውድነቱ እንዲታመሱ በማድረግም ለኑሮ ውድነቱ በር ከፍተዋል። ሆኖም አሁን ሊበቃቸው ይገባል። ለዛሬ ህዝቡን የአለአግባብ መዝብረው ያገኙት ኃብት ነገ ይብሉት አይብሉት እርግጠኞች አይደሉም።

ወሎ ማንም የተቸገረ ሰው መጥቶ ጠግቦ የሚመለስባት ምድር እንጂ። ይህንን ደግሞ ከጦርነቱ በኋላም መድገም ያስፈልጋል። አንዳንድ የውሸት ፕሮፖጋንዳ የሚነዙ ሰዎችን መቀበልን መተው አለብን። በፍራቻ ሕዝቡን ከማሸበር ይልቅ እንዲሰራ ማበረታታት ላይ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀስም ይገባል። የዚህን ጊዜ ጦረኞችን ድል እንነሳቸዋለን። ይህንን ለማድረግ ቁርጠኛ እንሁንም ስትል ትመክራለች።

ወሎ እንግዳ ተቀባይ አገር ነው። ሴቶች ደግሞ ለዚህ ግንባር ቀደም ናቸው። መቀነታቸውን ፈተው፤ ቤት ያፈራውን አራግፈው እንግዳ ይቀበላሉ። ጦርነት ቤታቸውን ቢያራቁተውም ዛሬም የወለዬዎች እንግዳ ተቀባይነት አልነጠፈም።

አሁን ላይ የልብ ስብራቱ የአንድ አካል ብቻ አይደለም እንደአጠቃላይ ጦርነት በተካሄደባቸው ቦታዎች ሁሉ ያለ ነው። እናም ያንን ለማከም በልቶ ማደር ላይ በቅድሚያ መሥራት ያስፈልጋልና የቀደመውን የገበያ ድምቀት መመለስ ላይ መረባረብ አለብን። ተረጋግቶ የሚሰራ ማህበረሰብ እንዲኖርም ሕወሓት የሚፈልገውን የሽብር ወሬ ማራገብ የለብንም። ምክንያቱም ይህ ለእርሱ እንጂ ለእኛ ምግብ አይሆነንም ብላለች።

ጦርነቱን ከእነጣለው ጠባሳ መመከት የሚቻለው በአንድ ነገር ብቻ እንደሆነ የምትጠቁመው ስመኝ፤ በአንድነታችን ጠንክረን ችግራችንን በጋራ ስንፈታው ብቻ ነው። በተለይም ያልባሰበት ወደ ባሰበት ማየት ከምንም በላይ ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ በጦርነቱ ቤተሰብ ያልሞተበት፤ ያልተሰቃየበትና ያልታመመበት አለ ለማለት ያስቸግራል። ይህንን ማዳንና ወደቀደመ ማንነት መመለስ የሚቻለው ጉዳቱ የአንዱ ብቻ ነው ብሎ ባለመውሰድ ነው። የወንድሜ ሕመም የእኔም ነው ማለት ይገባል። የተጎዳን የተጎዳ ነውና ማከም የሚችለው ይህንን እናድርግ ምክሯ ነው።

ጦርነቱና ሴቶችን በተመለከተ የሴቶች መብት ተሟጋች፤ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ለጾታዊ ጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ሴቶች ከለላ፤ የምክርና ሌሎች አገልግሎቶችን በመስጠት የሚታወቀው የሴቶች ማረፊያ እና ልማት ማህበር መሥራች እና ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የሕግ ባለሙያዋ ወይዘሮ ማሪያ ሙኒር በአንድ ወቅት ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ያሉትን እናንሳና ሀሳባችንን እናሳርግ።

ኢትዮጵያ ውስጥ በጦርነት ሳቢያ የጥቃቱ ሰለባዎች ቁጥር ጨምሯል ወይም ቀንሷል ለማለት የተጠና የለም። ነገር ግን ከጦርነቱ በኋላ በጓዳ ይቀር የነበረው ችግር አደባባይ እየወጣ በመሆኑ መጨመሩን ያሳየናል። ሌላው ጦርነት ባለበት አካባቢ ሴቶች ለጾታዊ ጥቃት የመጋለጥ ምጣኔ እንደጨመረ የሚያሳየው ደግሞ በየሆስፒታሉ የሚታየው የተጎዱ ሴቶች ብዛት ነው። የሚያደርሰው ጥቃት ከጦር መሣሪያ ከባድ ምት እንደማይተናነስ አይተናል ይላሉ።

የሴቶችን ጥቃት ግጭት ፈጣሪዎች ሳይቀሩ ይጠቀሙበታል የሚሉት የሕግ ባለሙያዋ፤ የጥቃቱ ነገር ገና በጣም ብዙ ሥራ እንደሚፈልግ ያነሳሉ። ለዚህም ማህበራቸው በርካታ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝም ይናገራሉ። ለዚህም እንደማሳያ የጠቀሱት ለሦስት ወራት በተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው መጎብኘታቸውንና አቅም በፈቀደ አስፈላጊውን የምክር እና የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረጋቸውን ነው። ደሴ እና ወልደያ በሚገኙት በአቋቋሟቸው ማረፊያ ቤቶች ከአንድ ሺህ በላይ ሴቶችን ማገዝ እንደቻሉም ያስረዳሉ። ይህ ጦርነት በጣም አስከፊና ሰውን ለመርዳት እንኳን ያልተቻለበት ነው። እናም ያለማህበረሰቡ እገዛ ብዙዎች መዳን አይችሉምና ማህበረሰቡ በትንሹ እንኳን ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶችን መንከባከብ መቻል አለበት። እኛም ምክራቸውን እውን አድርገን አገራችንን እናሻግራት በማለት ለዛሬ አበቃን። ሰላም!!

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ትናንት በተጠናቀቀውና በአሜሪካ ኦሪገን ባለፉት አስራ አንድ ቀናት ሲካሄድ በቆየው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በድል ላይ ድል ደርበዋል። አሜሪካንን ተከትለውም ከአለም ሁለተኛ ሆነው ያጠናቀቁበትን 4 የወርቅ፣4 የብርና 2 የነሐስ ሜዳሊያ አስመዝግበዋል። በዚህም የኢትዮጵያ ስም በአትሌቲክሱ መንደር ገናና ሆኗል። ሰንደቅአላማዋም ከፍ ብሎ ተውለብልቧል። ሕዝብም ተደስቷል። ስለሩጫ ስናነሳ ፈር ቀዳጁ አበበ ቢቂላ ነው። አበበ በሮም የመጀመሪያ ድሉን ቀጥሎም በቶኪዮ ኦሊምፒክ ሁለተኛ የማራቶን ክብሩን ተቀዳጅቷል። አበበ ሁለተኛውን ድል ሲያስመዘግብ በወቅቱ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ድሉን ሮይተርስን ጠቅሶ ያስነበበውን ዘገባ አካተናል። ከአደጋ ከወንጀልና ከልማት ነክ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ዘገባዎችም አሉን።

### አበበ ቢቂላ ለሁለተኛ ጊዜ አሸናፊ ሆነ

ቅልጥሞቹ እንደ ብረት የሚጠነክሩት ኢትዮጵያዊው አበበ ቢቂላ በቶኪዮ የማራቶን ውድድር ከሚደረግበት ሥፍራ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ይታይበት የነበረው ፈገግታ ፍጹም አልተለወጠም ነበር ሲል ሮይተርስ አስረድቷል። የአበበ አሸናፊነት በዓለም መዝገብ ውስጥ እስከ ዘላለም የሚኖር ቋሚ ትዝታ አትርፏል። አበበን በየመንገዱ ከ፪ ሚሊዮን ፭፻ሺህ ሕዝብ በላይ ተሰልፎ የጋለ ስሜቱን ይገልጥለት ነበር።

በ፲፰ ኛው የኦሎምፒክ የማራቶን ውድድር፣ አበበ ቢቂላ ለሁለተኛ ጊዜ በማሸነፍ የወርቅ ሜዳሊያ አግኝቷል። አበበ ቢቂላ እስከ ዛሬ ድረስ ተደርጎ የማይታወቅ የማራቶን ውጤት ከማስገኘቱም በላይ፣ አንድ ሰው ሁለት ጊዜ በመድገም የማራቶን አሸናፊ የሆነ እስካሁን ድረስ በዓለም እንደሌለ ሮይተርስ ባስተላለፈው ወሬ ገልጧል።

አበበ የቶኪዮውን ማራቶን ሩጫ ያሸነፈው፣ በ2ሰዓት ከ12 ደቂቃ ከ11.2 ሰከንድ ሲሆን፣ በሚሮጥበት ጊዜ ተወዳዳሪ የሆኑት ፷፰ ሯጮች በሙሉ ሩጫው ከተጀመረበት አንስቶ እስከ ፍፃሜው ድረስ በመምራት ሁለተኛ የሆነውንና ፩ ሺህ ሜትር ያህል ቀድሞት ገብቷል። አበበ ግዴታውን ማለት ፵፪ ኪሎ ሜትር ከ፩፻፺፭ ሜትሩን ጨርሶ አላረፈም። መቼ ሥራ ፈታና ሰውነቱን በማፍታታት ልዩ ልዩ ዓይነት ጅምናስቲክ በመሥራት ጓደኞቹን ሲጠብቅ ነበር።

የማራቶን ውድድር ለመመልከት ከ፸ሺህ ሕዝብ በላይ ተገኝቶ አበበን በማድነቅ በደመቀና በጣም በሚያስተጋባ ጭብጨባ ደስታውን በመግለጥ የሚሠራውን ጅምናስቲክ ተመልክቷል።

አበበ ቢቂላ ከሮም አሸናፊነቱ በኋላ ወደ ልዩ ልዩ አገሮች ተጋብዞ በመሄድ እየሮጠ አሸናፊነቱን በሚገባ አስመስክሯል።በግብዣ የሮጠባቸው አገሮች ቼኮስላቫኪያ፣ አሜሪካ፣ ዑጋንዳ፣ ስፔን፣ ጃፓንና የቀሩትም አገሮች ናቸው።

የሃምሳ አለቃ አበበ ቢቂላ የቶኪዮን ማራቶን ከማሸነፉ ፴፫ ቀን በፊት (መስከረም 6 ቀን 1957) በትርፍ አንጀት ምክንያት በሀገሪቱ ሆስፒታል ኦፐራሲዮን ተደርጎለት ነበር።

(ጥቅምት 12 ቀን 1957 የታተመው አዲስ ዘመን )

### በከሰል ጭስ ሁለት ሴቶች ሞቱ

በዚህ ሰሞን ሁለት ሴቶች በአዲስ አበባ ባቡር ጣቢያ አካባቢ በከሰል ጢስ ምክንያት የሞት አደጋ ደርሶባቸዋል።

እንዲሁም ሌላ ፫ኛ ሴት የዚሁ አደጋ ደርሶባት ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ከገባች በኋላ፣ የህክምና ዕርዳታ ተደርጎላት ለመዳን ችላለች።እነዚሁ ፫ ሴቶች በግርድና ተቀጥረው ይሠሩ እንደነበረና የሚኖሩትም ቀጣሪያቸው በሰጡዋቸው ጠባብ የግንብ ቤት ውስጥ መሆኑ ተገልጧል። ከሞቱት ውስጥ አንደኛዋ በቤት ውስጥ ሞታ ስትገኝ፣ ሁለተኛዋ ግን ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ስትደርስ በሕክምና ለመረዳት ከሚቻልበት ደረጃ ያለፈች ስለነበር ሞታለች።

(መስከረም 8 ቀን 1957 የታተመው አዲስ ዘመን)

### የገንዘብ ቁጠባ ማኅበር ፶ ቤቶች ሠርቶ ያስረክባል

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የመኖሪያ ቤትና የገንዘብ ቁጠባ ማኅበር በዚህ ዓመት ከ፴ እስከ ፶ የሚደርሱ መኖሪያ ቤቶች በ1,000,000 ብር ሠርቶ ለሕዝብ እንደሚያስረክብ የማኅበሩ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ጌታቸው ተሰማ በሰጡት ወሬ ለመረዳት ተችሏል።

ማኅበሩ 600,000 ብር ተቀማጭ ሲኖረው ባለፈው ፶፮ ዓ.ም ፳፭ ቤቶች አስጀምሮ ዘጠኙን ጨርሶ ሲሰጥ፣ ለማሠሪያው 500,000 ብር ወጪ ማድረጉ ተገልጧል። እንዲሁም ባለፉት ሦስት ወራት ፩፻፳፯ ሰዎች 200,000 ብር በመክፈል የማኅበሩ አባል ሆነዋል።በጠቅላላው የማኅበሩ አባሎች ፱፻፳፯ መድረሳቸውን ወሬው አስረድቷል።

በጥንቱ ኤሮፕላን ማረፊያ በነበረው 100,000 ስኩየር ሜትር ቦታ ላይ ለልዩ ልዩ ቤተሰቦች መኖሪያ ቤቶች እንዲሠሩ ፕላን መውጣቱ ታውቋል።

ማኅበሩ ከላይ የተጠቀሰውን አንድ ሚሊየን ብር የሚያገኘው ባለፈው ዓመት በ500,000 ብር ካሠራቸው ቤቶች ከሚያስገባው ወለድና የብድር ተመላሽ ሲሆን ቀሪውን 100,000 ብር አበድሮ ወለዱን በመቀበል ነው ሲል በተጨማሪ አስገንዝቧል።

(መስከረም 12 ቀን 1957 የታተመው አዲስ ዘመን)

### ያልተመረመሩ ከብቶች ያረዱ በ6 ወር እስራት ተቀጡ

አዲስ አበባ፣(ኢ-ዜ-አ-) አቶ ሰይድ ዋቅቶሌ የተባሉ የአዲስ አበባ ከተማ ኗሪ በመጋዘናቸው ውስጥ ሽታው የአካባቢውን ሕዝብ ጤና የሚያውክ ርጥብና ደረቅ ቆዳ ከማጠራቀም አልፈው፣ ጤንነቱ ያልተመረመረ ከብት በዚሁ ግቢ ከሕግ ውጪ እየደጋገሙ በማረዳቸው በስድስት ወር እስራት እንዲቀጡ የተፈረደባቸው መሆኑን ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የተገኘው ዜና ገለጠ።

አቶ ሰይድ ዋቅ ቶሌ በአካባቢው ኗሪና እንዲሁም በጠቅላላው ሕዝብ ጤንነት ላይ ጠንቅ የሚያስከትሉን ድርጊቶች የፈጸሙት አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ፫ ጊዜ መሆኑንና በዚህም ከ፳ ብር እስከ ፩፻፶ ብር ተቀጥተው እንደነበረ ዜናው ገልጧል።

አቶ ሰይድ ዋቅቶሌ ፍርድ ቤት ቀርበው የሰጡት መከራከሪያ ማስረጃ "በገዛ ርስቴ ላይ ፣የፈለግሁትን ብሠራ አልከለከልም" የሚል ብቻ እንደነበርና ፍርድ ቤቱም በገዛ ርስት ላይ ተቀምጦ ሕዝብን የሚጎዳ ሥራ መሥራት በሕግ የሚያስጠይቅ ሥራ መሆኑን ገልጦ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር ፰፻-፺፻፳፬ በተከሳሹ ላይ የ፮ ወር እስራት መፍረዱን የአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የማስታወቂያ ክፍል ገልጧል።

አቶ ሰይድ ዋቅ ቶሌ የእስራት ጊዜያቸውን እንደጨረሱ የቆዳ መጋዘናቸውን የሕዝብ መኖሪያ ከሆነው አካባቢ አንስተው ለኢንዱስትሪ በተመደበው ቀበሌ ካላዛወሩ በቀር ባሉበት ቦታ ላይ እንዳይገለገሉበት ፍርድ ቤቱ በተጨማሪ ጥብቅ ትዕዛዝ መስጠቱ ታውቋል።

(ሐምሌ 3 ቀን 19 62 ከወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

# ዓለም አቀፍ



## ህጋዊ ሰነድ የሌላቸው አንድ ሺህ 200 ስደተኞች ጣሊያን ደሴት ደረሱ

የጣሊያን መንግሥት ባለፉት 24 ሰዓታት ውስጥ ብቻ ወደ 1 ሺህ 200 የሚጠጉ ሕጋዊ ሰነድ የሌላቸው ስደተኞች ጣሊያን መግባታቸውን ገለፁ። ከተለያዩ የእስያ፣ የአፍሪካ እና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት የተውጣጡ ስደተኞች ሲሲሊ ወደቦች በጀልባዎች ተጭነው ደርሰዋል።

ባሳላፍነው ቅዳሜ እና እሁድ ወደ ጣሊያን የገቡት ስደተኞች ከአፍጋኒስታን፣ ፓኪስታን፣ ሱዳን፣ ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ የመጡ መሆናቸውን በነፍስ አድን ተግባር ላይ የተሰማሩት ሰዎች ገልጸዋል። ባለስልጣናቱ እንዳሉት በካላብሪያ የባህር ዳርቻ ብቻ 674 ሰዎችን የተቀበሉ ሲሆን፣ አምስት አስከሬኖችም ከስደተኞቹ ጋር በሰው በተጨናነቁት የአሳ ማጥመጃ ጀልባዎች ላይ ተጭነው ተገኝተዋል።

እንዲሁም በ15 ጀልባዎች ተጭነው የመጡ 522 ስደተኞች ባሳለፈነው ቅዳሜ ወደ ላምፔዱሳ ወደብ ደርሰዋል። ከሊቢያ እና ቱኒዚያ የተነሱት ጀልባዎች ወደ አውሮፓ ለመግባት የሚፈልጉ ሰዎች መዳረሻ ከሚያደርጓቸው ወደቦች መካከል አንዱ ወደ ሆነው ላምፔዱሳ ደርሰዋል።

የጣሊያን መገናኛ ብዙሃን እንደዘገቡት በሲሲሊ ደሴት የሚገኘው የስደተኞች ማዕከል ማረፊያዎች ባለፉት ሳምንታት ውስጥ በከፍተኛ መጠን ተጨናንቋል። ማዕከሉ ከሚችለው የ350 ሰዎች አቅም በላይ በአሁኑ ጊዜ 1 ሺህ 184 ሰዎችን በማስተናገድ ላይ ይገኛል። የባህር ዳርቻ ጥበቃ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በየዓመቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተጨማሪ ስደተኞችን ከባሕር ላይ ይታደጋሉ።

የሜዲትራኒያን ባሕር ለሕገ-ወጥ ፍልሰት በጣም አደገኛ ከሆኑ መንገዶች አንዱ ነው። እንደ የተባበሩት መንግሥታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን ከሆነ እ.ኤ.አ በ2021 በሜዲትራኒያን ባሕር እና በሰሜን ምዕራብ አትላንቲክ ውቅያኖስ ውስጥ ከ3ሺህ 200 በላይ ሰዎች ሞተው ወይም ጠፍተዋል ተብለው ተመዝግበዋል።

አደገኛውን ጉዞ ከሚያደርጉት መካከል ብዙዎቹ ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎች በሚያቀርቡላቸው ጊዜያዊ ጀልባዎች ላይ የሚሳፈሩ ሲሆን ጀልባዎቹ በጉዞ መሃል ሥራውቸውን በሚያቆሙበት ወቅት ሕገ-ወጥ የሰዎች አዘዋዋሪዎቹ ስደተኞቹን ባሕር ላይ ትተዋቸው እንደሚሄዱ የቢቢሲ ዘገባ ያመለክታል።

## ቱኒዚያውያን አዲስ በተዘጋጀው የሕገ መንግስት ረቂቅ ላይ የሕዝበ ውሳኔ ድምጽ ሰጡ



ቱኒዚያውያን በአዲስ መልኩ በተዘጋጀው የሕገ መንግስት ረቂቅ ላይ የሕዝበ ውሳኔ ድምጽ ሰጥተዋል። ለድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ በመላ አገሪቱ የሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ከጠዋቱ 12 ሰዓት ላይ መከፈታቸው ተመላክቷል።

የቱኒዚያ ፕሬዚዳንት ካይስ ሰኢድ የአገሪቱን መንግስት ካባረሩ እና ፓርላማውን ካገዱ በኋላ ቱኒዚያ በአዋጅ እንድትመራ ከወሰኑ ዛሬ አንድ ዓመት የሞላው መሆኑን አልጀዚራ በዘገባው አስታውሷል። የፕሬዚዳንቱን ውሳኔ ተከትሎም ስርዓቱን ወደ አንድ ሰው አገዛዝ ለመመለስ የተደረገ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ነው ሲሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሲተቹ ቆይተዋል።

ረቂቁ ለፕሬዚዳንት ካይስ ሰኢድ የበለጠ ስልጣን ከመስጠቱ ባለፈ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን ሚና እንደሚገድብ እና ቅቡልነት እንደሌለውም ተናግረዋል። ፕሬዚዳንት ካይስ ሰኢድ በበኩላቸው፥ በአገሪቱ በሙስና የተዘፈቀ የፖለቲካ ልሂቃንን ለመቆጣጠር ያደረጓቸው ለውጦች አስፈላጊ እንደሆኑ ነው የሚያስረዱት።

በሕዝበ ውሳኔው ለመሳተፍ 9 ነጥብ 5 ሚሊየን ሰዎች ድምጽ ለመስጠት የተመዘገቡ ሲሆን፥ በምርጫው ዕለት መራጮች በተሳሳተ የምርጫ ጣቢያ ተገኝተው ችግር መፍጠራቸው ተጠቁሟል። አዲሱ ሕገ መንግስት 10 ምዕራፎች እና 142 አንቀጾችን የያዘ እና ቱኒዚያ በፕሬዚዳንታዊ ስርዓት የምትመራ ሉዓላዊ ሀገር መሆኗን የሚደነግግ መሆኑን ኤፍቢሲ ዘግቧል።

# ስፖርት

# የወንዶች 5ሺ ሜትር ድል ዳግም ፊቱን አዙሯል

**ቦጋለ አበበ**

18ኛው የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከአስራ አንድ ቀናት በኋላ ትናንት በኦሪገን ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ በ4ወርቅ፣4ብርና 2 ነሐስ ሜዳሊያዎች አሜሪካን ተከትላ ከአለም ሁለተኛ ከአፍሪካ ደግሞ ቀዳሚ ሆና አጠናቃለች። አንጸባራቂ ድል በውድድሩ ያስመዘገበችው ኢትዮጵያ በውድድሩ ታሪክ ትልቁን ስኬት ተጎናጽፋለች። ባልተጠበቁ ርቀቶች ጭምር የተለያዩ ስኬቶችን ማግኘት የቻለችው ኢትዮጵያ ድል በተለመደባቸው የወንዶች 10 እና 5ሺ ሜትር አንድም ሜዳሊያ ማስመዝገብ አልቻለችም። በነዚህ ርቀቶች የተለመዱ ድሎች መመዝገብ አለመቻላቸው የበለጠ አንጸባራቂ ድል እንዳይመዘገብ ማድረጉም የስፖርት ቤተሰቡ መነጋገሪያ ሆኗል።

ኢትዮጵያ በተለይም በቻምፒዮናው ሁለተኛ ቀን ውሎ በ10ሺ ሜትር የርቀቱ ኮከብ አትሌቶቿ ሜዳሊያ ውስጥ መግባት አለመቻላቸው የሚያስቆጭ ቢሆንም ትናንት በውድድሩ ፍጻሜ እለት በተካሄደው የ5ሺ ሜትር ውድድር ይካካሳል የሚል ተስፋ ነበር። ያም ሆኖ ኢትዮጵያውያኑን የርቀቱ ኮከብ አትሌቶችን ጨምሮ ሌሎች በርካታ አትሌቶች ደካማ አቋም አሳይተዋል። ይህም ባለፉት ሁለት ቻምፒዮናዎች ኢትዮጵያ በወርቅ የደመቀችበት የርቀቱ ክብር ዳግም ፊቱን እንዲያዞር አድርጎታል።

ኢትዮጵያ በ5ሺ ሜትር ሴቶች ውድድር በአለም ቻምፒዮና መድረክ ያላትን የአለም ቀዳሚ ስኬት በወንዶች የላትም። በሴቶች ያላትን የስኬት የበላይነት ከትናንት በስቲያም በኦሪገን መድገሟ ይታወቃል። እ.ኤ.አ በ1991 ቶኪዮ የአለም ቻምፒዮና ላይ በፊጣ ባይሳ የብር ሜዳሊያ




**የአለም ቻምፒዮና የ5ሺ ሜትር ድል ከሁለት ቻምፒዮናዎች በኋላ ከኢትዮጵያውያን እጅ ወጥቷል፣**

የተጀመረው የኢትዮጵያ የርቀቱ ስኬት ወደ ወርቅ ለመሸጋገር ብዙ ጊዜ ፈጅቷል። ራሱ ፊጣ ባይሳን ጨምሮ እንደ ጀግናው አትሌት ሀይሌ ገብረስላሴ፣ ስለሺ ስህን፣ ሚሊዮን ወልዴና ሌሎችም ታሪካዊ አትሌቶች በሩጫው አለም የተለያዩ ርቀቶች መንገስ ቢችሉም ኢትዮጵያን በ5ሺ ሜትር ወደ ወርቅ ሜዳሊያ ማሸጋገር አልቻሉም። እ.ኤ.አ 2003 ሴንት ዴኒስ ላይ በነሐስ ሜዳሊያ የርቀቱን ክብር ያሟሸው የምንጊዜም የረጅም ርቀት ምርጥ አትሌት ቀነኒሳ በቀለ እ.ኤ.አ 2009 በርሊን ቻምፒዮና ላይ የርቀቱን የወርቅ ሜዳሊያ ታሪክ አንድ ብሎ ጀምሯል። ከዚያ በኋላ ግን አልደገመም። ኢትዮጵያም በርቀቱ ዳግም ወደ ወርቅ ሜዳሊያ ክብር ለመመለስ እ.ኤ.አ የ2017ቱን የለንደን ቻምፒዮና መጠበቅ ነበረባት። ከዚያ በፊት በነበሩ ቻምፒዮናዎች በዘመናቸው የርቀቱ ፈርጥ የሆኑ እንደ ሃጎስ ገብረህይወት አይነት አትሌቶችም ከብርና ከነሐስ የዘለለ ሜዳሊያ ማስመዝገብ አልቻሉም። ለንደን ላይ በወቅቱ ቁጥር አንድ የነበረውን ፋራህን በአገሩና በደጋፊው ፊት በማሸነፍ ወርቅ ያጠለቀው ድንቅ ኢትዮጵያዊ አትሌት ሙክታር ኢድሪስ ግን በቀጣዩም ቻምፒዮና 2019 ዶሃ ላይ ዳግም በወርቅ የደመቀበትን ታሪክ አኑሯል። ዛሬ ግን ይህ ታሪክ ሳይቀጥል ቀርቷል። የርቀቱ ከዋክብት የሆኑ የአለምና የኦሊምፒክ ቻምፒዮኖች ጭምር እጅግ ደካማ አቋም ባሳዩበት ውድድር አዲስ ቻምፒዮን ብቅ ብሏል። ታላላቆቹም አትሌቶች ለትንሿ አገር ኖርዌይ ወጣት አትሌት ጃኮብ ኢንግብሪግስተን ክብሩን አሳልፈው ሰጥተዋል። ኬንያዊው ጃኮብ ክሮፕና ዩጋንዳዊው ኦስካር ቼሊሞ ታላላቆቹ የርቀቱ ፈርጦች በሙቀት በተፈተኑበት ውድድር ብርና ነሐስ አምጥተዋል። የርቀቱም የአፍሪካውያን ዙፋን ተገርስሶ ከሁለት ቻምፒዮናዎች በኋላ ዳግም ወደ አውሮፓ አምርቷል።

ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም በርቀቱ 3ወርቅ፣ 6 ብርና 4 ነሐስ አስመዝግባለች። ትውልደ ሶማሊያዊው የእንግሊዝ አትሌት ሞሐመድ ፋራህ እ.ኤ.አ ከ2011 እስከ 2015 ድረስ በተከታታይ ቻምፒዮናዎች ወርቅ ያጠለቀ አትሌት ብቻ ሳይሆን በርቀቱ ሦስት ጊዜ በማሸነፍም የሚስተካከለው የለም። ፋራህ በርቀቱ አንድ የብር ሜዳሊያ ያጠለቀበት ታሪክም አለው። እሱን ተከትሎ ኬንያዊው አትሌት ኢስማኤል ኪሩይ ሁለት ወርቆችን በማሸነፍ የሚጠቀስ ሲሆን ኢትዮጵያዊው ሙክታር ኢድሪስ ባለፉት ሁለት ቻምፒዮናዎች ይህን ታሪክ የሚጋራበትን ድል ማስመዝገቡ ይታወቃል።

ኬንያ በርቀቱ በወርቅ ሜዳሊያ ብቻ ሰባት ጊዜ በማሸነፍ የአለም እጅግ ስኬታማዋ አገር ነች። የቻምፒዮናው ክብረወሰንም በኬንያዊው ድንቅ አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ እ.ኤ.አ 2003 ሴንት ዴኒስ ላይ 14:26:72 የተያዘ ሲሆን እስካሁንም የሚደፍረው አልተገኘም።

## አማራ ክልል

ለአቶ ገብረሥላሴ አሻግሬ ባሉበት፡- ከሳሽ ገ/ህይወት አዳሙ፣ ተከሳሽ፡- ገብረስላሴ አሻግሬ መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰስዎን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልስዎን ለቀን 28/11/2014 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ 3፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካባቢ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ባ/ዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

በከሳሽ/ይግ/ባይ ፈይሣ ገ/ህይወት /አምባሉ ተዘራ ተከሳሽ/መ/ሰጭ ተመስገን ተስፋ አወቀ መካከል ስላለው የገንዘብ ክርክር ጉዳይ ለተከሳሽ የፍ/ቤቱን መጥሪያ ለመስጠት አድራሻቸው ሊገኝ ባለመቻሉ በዚህ ማስታወቂያ እንዲጠሩ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ በሰጠው መሰረት ተከሳሽ በቀጠሮው ለመስከረም 26 ቀን 2015 ዓ.ም. ማዕ/ጎን/ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ቢሮ ቁጥር 26 በ4፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በማዕከላዊ ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ባሳዝነው ዘውዱ ለገሰ የሰሌዳ ቁጥር 01- A19775 ኦሮ የሞተር ቁጥር፡- AFZWDB21073 የሻንሲው ቁጥር፡MD2A 25BZ2DWB57603 የሆነ ከላይ የተጠቀሰው ባለንብረት ተሽከርካሪ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ ጠፋብኝ ብለው በ 12/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ እና ታርጋ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዞዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ትራንስፖርት ባለሥልጣን የቢሾፍቱ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ባለሥልጣን**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና በተከሳሽ ደስታ ሞገስ አክሊሉ መካከል ስላለው ሙስና ወንጀል ክስ ጉዳይ ቀነ ቀጠሮ በ28/11/2014 ዓ.ም ሲሆን በ4፡00 ሰዓት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ ወንጀል ችሎት እንድትቀርቡ የማትቀርቡ ከሆነ ግን ክሱ በሌላችሁበት ታይቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን አውቃችሁ በዕለቱ እንድትቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

ከሳሽ ፌ/ጠ/ዐ/ህግ እና ተከሳሽ አበበ ታፈረ ካሴ መካከል ባለው የኮንትሮባንድ የወንጀል ክስ ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ29/11/2014 ዓ.ም 4፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት 9ኛ ገቢዎች እና ጉምሩክ ወንጀል ችሎት እንዲቀርቡ ካልቀረቡ ጉዳዩ በሌሉበት እንደሚቀጥል ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ እና በአድማኤ የሰሌዳ ቁጥር ዕድ-35-5851 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H8G7P33945 ሞዴል NPR6SNየሞተር ቁጥር 4HG1-535680 የሊብሬ ቁጥር 0138353 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እ እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ መርጃ ማእከል (በአድማኤ) የሰሌዳ ቁጥር ዕድ-35-2590 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A135G7102917 ሞዴል FSR. የሞተር ቁጥር 6HH1-488757 የሊብሬ ቁጥር 0184822 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ14/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የበጎ አድራጎት ማህበር የሰሌዳ ቁጥር ዕድ-35-6637 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNB3MA717740 ሞዴል 773257N3447A የሞተር ቁጥር WD615. 69*201107020727* የሊብሬ ቁጥር 281821/0262951 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ14/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የሠሌዳ ቁጥር ዕድ-35-2288 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNC3FD115267 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69*151017000447 የሊብሬ ቁጥር 0160501 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የሠሌዳ ቁጥር ዕድ-35-2227 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር LZZ5ELNCXFD115265 ሞዴል ZZ3257N3447A የሞተር ቁጥር WD615.69*151017000487* የሊብሬ ቁጥር 0160505 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 አመልክተዋል፡፡የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የሠሌዳ ቁጥር ዕድ-35-2526 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JALK6A136G7102912 ሞዴል FSR. የሞተር ቁጥር 6HH1-488740 የሊብሬ ቁጥር 0184812 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም መቄዶንያ የአረጋውያን እና የአእምሮ ሕሙማን መርጃ እና በአድማኤ የሠሌዳ ቁጥር ዕድ-35-5850 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAKP34H1G7P34287 ሞዴል NPR71 የሞተር ቁጥር 4HG1-537038 የሊብሬ ቁጥር 0138347 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ13/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቂርቆስ ቅ/ጽ/ቤት**